# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽሕፈት ለማስተማር የሚጠቀሟቸው የማስተማር ዘዴዎች ንጽጽር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአየር ጤና እና በክሩዝ 2ኛ ደረረጃ ት/ቤቶች

በ

እጅጋየሁ ተሾመ

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽሕፈት ለማስተማር የሚጠቀሟቸው የማስተማር ዘዴዎች ንጽጽር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአየር ጤና እና በክሩዝ 2ኛ ደረረጃ ት/ቤቶች


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዮማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ የሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለተግባራዊ ስነ ልሳን መለኮት አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

እጅጋየሁ ተሾመ


መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂዮማኒቲስ፤ ቋንቋዎች ጥናት ፤እና ጋዜጠኝነት ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

# የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽሕፈት ለማስተማር የሚጠቀሟቸው የማስተማር ዘዴዎች ንጽጽር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአየር ጤና እና በክሩዝ 2ኛ ደረረጃ ት/ቤቶች

**በ**

**እጅጋየሁ ተሾመ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| የአማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ______________ | ______________ | ______________ |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ | ______________ |

## ምስጋና

ከሁሉም በፊት ምህረቱን ቸርነቱንና ጥበቃውን ከእኔ ላላራቀውና ለረዳኝ ፈጣሪ እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይገባዋል፡፡ ለዚህም ጥናት መሳካት ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ የማማከር አገልግሎት ከመልካም ትህትና ጋር እስከ ጥናቱ መጨረሻ እልባት ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታቸው አዱኛ ከታላቅ አክብሮት ጋር ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ለአየር ጤና እና ክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን፤ተማሪዎች እና አስተዳደር ሰራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ የጥናቱን ወጪ በመሸፈን ለተባበረኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ሲያመኝ በመንከባከብ እና እርዳታ እያደረጉልኝ ለዚህ ውጤት ስላበቁኝ ልባዊ ምስጋናዬን እቀረብኩ እንዲሁም ለቤተሰቦቼ እና ለጓደኞቼ በልኡል እግዚአብሔር ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግልና የመንግስት ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት ወቅት የትኞቹ መምህራን የማስተማር ዘዴ ጥሩ አተገባበር እንዳላቸው በመፈተሽና በመለየት ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው። በዚህ ጥናት የተመረጡት በ 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመንግስትና በግል ት/ቤት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምተሩ መምህራን ናቸው። በመስተዳደሩ ከሚገኙት መምህራን መካከል በዚህ ጥናት አንድ የመንግስት እና አንድ የግል ት/ቤት ተመርጠዋል። ጥናቱ በሚካሄድባቸው ት/ቤቶች በተመረጠው የክፍል ደረጃ ከሚያስተምሩ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች አራት ከግል ት/ቤት አራት በድምሩ ስምንት መምህራን እንዲሁም ከግል ት/ቤቶች 40 ከመንግስት ት/ቤቶች 40 በድምሩ ሰማኒያ ተማሪዎች በክፍል ምልከታ እና የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ ሰጪነት ተካተዋል። ጥናቱ የተከተለው የአጠናን ስልት አይነታዊና እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገለጻ ስልት ትንታኔ በመስጠት ነው። የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ የተሰበሰበባቸው መሳሪያዎች ናቸው። በዚህ መሰረት ከክፍል ምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በባለሙያ በመታገዝ በSPSS ተሰርቷል። በመሆኑም ምልከታ የተገኘ ውጤት በመንግስት ት/ቤት 3.797 ፤ በግል ት/ቤት 4.395 አማካኝ ውጤት ያለ ያስመዘገቡ የተማሪዎች የግምገማ ውጤት ደግሞ የመንግስት ት/ቤቶ 3.809፤ የግል ት/ቤት 4.25 አማካኝ ውጤት አስመዝግበዋል። በመምህራን መካከል ጽሕፈት በማስተማር ዘዴ የጎላ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገው ስሌት በክፍል ውስጥ ምልከታ የቴ- ስሌት ዋጋ 3-435 ሲሆን የቴ- የቴ- ጣሪያ ዋጋ ደግሞ 2-542 ነው። የተማሪዎች ግምገማ የቴ-ስሌት ዋጋ 4-320 ሲሆን የቴ-ጣቲያ ዋጋ ደግሞ 2-352 ነው። ከተገኘው ውጤት መረጃ በመነሳት የቲ - ስሌት ዋጋ ከቲ ጣሪያ ከበለጠ በመምህራን ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን እንረዳለን። በዚህም አማካኝ ስሌት ሆነ የቴ-ስሌት ውጤት በመንግስት ት/ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ት/ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ውጤት በልጦ በመገኘቱ የግል ት/ቤት መምህራን የተሻለ አተገባበር ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ለዚህም ምክንያቱ የመምህራን እቅድ አዘገጃጀት ለተማሪዎች የግል መመሪያ መስጠት፤ አፋጣኝ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ፤ ማስተማሪያ ዘዴ ወዘተ..መሆኑን መረዳት ተችሏል። ከተለዩት ችግሮች በመነሳት መመህራን ጽህፈት ለማስተማር ዘዴ ከማስተማር ሲያቅዱ በግል ማስተማሪያዎች እንደሚጠቀሙባቸው፤ የጽህፈት ችሎታን የሚያግዙ የተለያዩ መልመጃዎችን መስጠት እንደሚገባ ወዘተ.. የሚሉ አስተያየቶችም በጥናቱ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል።*

# ማውጫ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ........ ii

የሠንጠረዥ ማውጫ ........ v

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ........ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 4

1.6. የጥናቱ ውስንነት ........ 4

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........ 5

2.1 የጽሁፍ ምንነት........ 5

2.1.2 የጽህፈት ትምህርት ባህሪያት ........ 7

2.1.3 የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች........ 9

2.1.3.1 ስነ ልቦናዊ ባህርይ ........ 9

2.1.3.2 ስነ ልሳናዊ ባህርይ ........ 10

2.1.3.3 አእምሮአዊ ባህርይ ........ 10

2.2 የጽህፈት የማቀድና ማስተማር መርሆዎች ........ 11

2.3 የጽህፈት ክሂል ትምህርት ማስተማሪያ አቀራረቦች........ 12

2.3.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ........ 12

2.3.2 ሒደት -ተኮር አቀራረብ ........ 13

2.3.3 ጃነር ጽኁፈት ማስተማሪያ አቀራረብ ........ 14

2.3.4 ሒደት ወ ጀነር ጽህፈት ማስተማሪያ አቀራረብ ........ 15

2.4. በፅህፈት ትምህርት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ........ 16

2.4.1. የግል ግምገማ ........ 17

2.4.2. ጓደኛ ምጋቤ ምላሽ ........ 17

2.4.3. የመምህር ምጋቤ ምላሽ ........ 17

2.4.4. የመምህር ተማሪ ምክክር ምጋቤ ምላሽ ........ 17

2.5. የመጻፍ ክሂል ምዘና ........ 18

2.5.1. ሆልስቲክ መመዘኛ መስፈርት ........ 18

2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 19

**ምዕራፍ ሦስት**

የአጠናን ዘዴ........ 21

3.1 ናሙና አመራረጥ ........ 21

3.1.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ ........ 21

3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 21

3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 22

3.1.4 የመምህራን አመራረጥ ........ 22

3.1.5 የተማሪዎች አመራረጥ ........ 23

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 23

3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 24

3.2.2 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ........ 25

3.2.3 የመምህሩን ፅሁፍ መጠይቅ ........ 26

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 26

ምዕራፍ አራት


የመረጃ ትንተና ........ 28

4.1 የተጠኚ መምራን እና ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ ........ 29

4.2 ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 31

4.3 ከክፍል ምልከታና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 36

4.3.1. የመምህሩ የፅህፈት ትምህርት እቅድ ........ 37

4.3.2 የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ስለመስጠት ........ 39

4.3.3 የመምህሯ ፅህፈትን ለማስተማር ግልፅ መመሪያ ስለመስጠት ........ 40

4.3.4 የመምህሩ/ሯ የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዥ ........ 42

4.3.5 የመምህራን ግብረ መልስ አሰጣጥ ........ 43

4.4 በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን የፅህፈት ማስተማር ዘዴ ውጤት ........ 45

4.4.1. የፅህፈት ትምህርት አተገባበር ውጤት ........ 45


ምዕራፍ አምስት


ማጠቃለያ እና አስተያየት ........ 49

5.1 ማጠቃለያ ........ 49

5.2 አስተያየት ........ 51

ዋቢ ፅሁፎች ........ 53

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መረጃ........................................................................29
ሰንጠረዥ 2 የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ  ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ ........................................30
ሠንጠረዥ 3 የመምህራን የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴ አጠቃቀም.........................................31
ሰንጠረዥ 4 ስለ ጽሑፍ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ እውቀት መኖር ..........................................32
ሰንጠረዥ 5 የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን እንዲጽፉ ማድረግ...............................................33
ሰንጠረዥ 6 በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን እሰጣለሁ፡፡ ............................................34
ሰንጠረዥ 7 ለተማሪዎች በወቅቱ ምጋቢ ምላሽ ስለመስጠት ...............................................35
ሰንጠረዥ 8 የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል መመዘን፡፡ ...............................................36
ሠንጠረዥ 9 የመምህራን ትምህርት እቅድ አያያዝ አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት...................37
ሠንጠረዥ10ለተማሪዎችየፅህፈትችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን መስጠት አማካይና ቲ-ስሌትውጤት..39
ሠንጠረዥ 11 መምህሩ/ሯ ግልፅ መመሪያ መስጠት አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት ................41
ሠንጠረዥ 12 የመምህሩ/ሯ የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት...42
ሠንጠረዥ 13 ግብረ መልስ አሰጣጥ አማካኝና ቲ-ስሌት ውጤት.......................................43
ሰንጠረዥ 14 የመምህራን የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ አማካይና የቱ- ስሌት አጠቃላይ ዉጤት ..........................................................................................................45
ሰንጠረዥ 15 የምልከታ ተማሪዎች ግምገማ አጠቃላይ ውጤት .........................................47

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ጽሕፈት በአግባቡ ለመግባባትና የተፃፈውንም አንባቢ በቀላሉ ይረዳ ዘንድ ለመፃፍ የሚያስፈልጉትን ተግባራቶች ማወቅ ተገቢ ነው።ተግባራቱም የሀሳብ አደረጃጀት ፣የአንቀፅ አመሰራረት፣የአረፍተነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ለመፃፍ ክሂል ወሳኝ እውቀቶች እንደሆኑ ማረው (1988) ይገልፃሉ።

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ መጻፍ ነው። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ደግሞ ብዙ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል። የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም እንዲሁም የዓረፍተ ነገር አወቃቀር እና የአንቀጽ አመሰራረት ለክሂሉ በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

የመጻፍ ክሂልን በትምህርትነት መስጠት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦች አገልግሎት ላይ ውለዋል። ይህን አስመልክተው Nunan (1991፣48) "ዋነኛ ዓላማውም ተማሪዎች የቋንቋ ህግጋት ላይ ተመስርተው የመጻፍ ክሂልን እንዲማሩ ማስቻል ነው። በዚህ አቀራረብ፣ የትምህርቱ ዓላማ ከግብ መድረሱ የሚረጋገጠው ተማሪዎች የሚጽፉትን የመጨረሻ ድርሰት በጥልቀት በማየት ነው።" በማለት ሀሳብ አቅርበዋል።

ተማሪዎች በስተመጨረሻ ከሚያዘጋጁት ጽሑፍ ይልቅ፣ ጽሑፉን ለማቀነባበር ለሚጠቀሟቸው ልዩ ልዩ ሂደታዊ ተግባራት ትልቅ ዋጋ ይሰጣል። ተማሪዎች ጽሑፉን ለማቀናበር የሚያልፏቸው ሂደቶች ለውጤታቸው ማማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይታሰባል። Raimes (1983) በትምህርቱ ሂደት የመምህሩ የበላይነት እና ጣልቃገብነት ሳይኖር፣ ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍጥነት እየተለማመዱ የመጻፍ ሥራቸውን ያከናውናሉ እንጂ፣ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት እንዲያስቡ የሚያደርግ አለመሆኑን ይገልፃሉ። ይህም አቀራረብ ምንም እንኳን መጻፍ ሂደታዊ ቢሆንም፣ ተማሪዎች በስተመጨረሻ በሚጽፉት ድርሰት ላይ ትኩረት አለመስጠቱ እና በሰዋስዋዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አለማድረጉ ትችት እንዲነሳበት ምክንያት ሆኗል Richard (1983)

ከሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ በኋላ የመጣው ዘውግ ተኮር ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ትኩረቱን ያደረገው የተለያዩ ዘርፎች ላይ መሰረት ያደረጉ ይዘቶችን በማምጣት ተማሪዎች የቋንቋውን መዋቅር፣ የማህበረሰቡን ተግባቦት ባገናዘበ መልኩ የትምህርቱን ሂደትን እንዲያከናውኑ ማስቻል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው ፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን የተለያዩ ታሪኮችን ፍቺ ለመስጠት ጥረት ቢያደርጉም፣ በራሳቸው እየፈጠሩ እንዲማሩ የመደረጉ ሁኔታ አነስተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ የተለያየ ቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓትን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በመምህሩ የሚሰጠው ገለጻ ሰፊ መሆኑ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ትችት እንዲነሳበት ምክንያት ሆኗል በማለት Raimes (1983)፤ እና Hyland (2003) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ተግባር ተኮር ፅህፈት ማስተማር ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ አውለዋል የሚባሉት ምሁራን ሲሆኑ፣ ጊዜውም በ1970ዎቹ አካባቢ ነበር፡፡ አያይዘውም፣ Prambu (1999) ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማርን የተጠቀሙት በህንድ፣ ባንጋሎር ውስጥ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ መሆኑንና በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥም ተግባቦታዊ ማስተማርን የተከተለ ፕሮጀክት ማከናወን እንደቻሉ Willis (2005) ያስረዳሉ፡፡

## 1.2. **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**

ከመጻፍ ክሂል ጋር በተያያዘ በርካታ ጥናቶች ለረጅም ጊዜያት እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ መጻፍ፣ የአፍልቆት ክሂል እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ወዘተ... እንዲገልጹ እና ልዩ ልዩ ልምምዶችን እንዲያከናውኑ የሚጠይቅ ክሂል ሲሆን፣ ክሂሉን ለማሻሻል ብዙ ጥረትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ተማሪዎቹ በክሂሉ ውስጥ ያሉትን አላባውያን (ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ሥርዓተ አጻጻፍን) በተግባር መለማመድ ስላለባቸው ነው (Nunan 1991) ፡፡

በመሆኑም ክሂሉ በትምህርትነት ሲሰጥ ከተማሪዎቹም ሆነ ከመምህሩ የሚጠበቁ ልዩ ልዩ ተግባራት አሉ፡፡ በተለይም ተማሪዎች ክሂሉን በተሻለ መልኩ ለማዳበር ሰፊ ልምምድ እና ብዙ የቃላት አጠቃቀም፣ የሀሳብ ተለጣጣቂነት እና ግጥምጥምነት፣ ወዘተ...ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ሲማሩ የተለያዩ ችግሮች ይስተዋልባቸዋል፡ አንደኛ፣ በተማሪዎች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች ከቋንቋ ችሎታ/ውጤታማነት እና ከግንዛቤ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ (ማሪው ፣1996) በአማርኛ ቋንቋ አውድ ላይ ተመስርተው

እንደሚገልጹት በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ በተማሪዎች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች እንዳሉ በመግለጽ፣ እነዚህንም ችግሮች በሶስት መልኩ ይመለከቷቸዋል፡፡ እነሱም፣ የሀሳብ እጥረት ወይም የሚጽፉትን ማጣት፣ የቋንቋ ችሎታ ማነስ እና ሀሳብን በአግባቡ ማደራጀት አለመቻል ናቸው፡፡

ሁለተኛ፣ ከመጻፍ ክሂል ጋር ተያይዞ በተማሪዎች ላይ የሚታዩ ችግሮች ከስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ስነልቦናዊ ችግሮች ከተማሪው/ዋ ውስጣዊ ስሜት የሚመነጩ ናቸው፡፡ ለዚህም እንደጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ነው፡፡ ተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ ጠንካራ የሆነ እምነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ጠንካራ እምነት መኖሩ ተማሪዎች ለትምህርቱ ሂደት ተነሳሽ በመሆን የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመቋቋም የተዋጣለት ጽሑፍ እንዲጽፉ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል በማለት ገልጸዋል (Bruning and Horn፣ (2000:114)

ሂደታዊ መርሀ ትምህርቶች ላይ መሰረት ካደረጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ ተግባር ተኮር የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴን በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል አኳያ የራሱ ሚና ይኖረው ይሆን? ተግባር ተኮር ስነፅሁፍ ማስተማር ዘዴ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ከተለምዶአዊው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረው ይሆን? እንዲሁም የመጻፍ ትምህርት ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገበር በአብዛኛው መምህር መራሽ መሆኑ፣ በተለያዩ ርዕሶች መጻፍ እንዲለማመዱ ያለማድረግ ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽንት ዝቅተኛ እደሂሆን መንስኤ ነው ብሎ አጥኝዋ ስላመነችበት ይህን ጥናት ለማጥናት አነሳስቷታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአየር ጤና እና በክሩዝ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስነፅሁፍ ማስተማር ዘዴን በንፅፅር መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የመምህራን የጽሕፈት ማስተማር ዘዴ የማስተማር አተገባበር ይፈተሻል፡፡
- የመምህራን የሚጠቀሙባቸውን የጽሕፈት ማስተማር ዘዴ በንፅፅር ይመረመራል፡፡
- ተማሪዎች መምህራን የሚጠቀሙባቸውን የጽሕፈት የማስተማር ዘዴ ምን ያህል ሥራ ላይ እንደሚያውሉት በመርመር ይፈትሻል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል።

- በአየር ጤና እና በክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎች እና ለመጽሐፍ አዘጋጆች ጽሕፈት ለማስተማር ስለሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ድክመትና ጥንካሬ መረጃ ይሰጣል።
- ጽሕፈት በማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህራን ሚና ምን መሆን እንዳለበት ትክክለኛውን አካሄድ ይጠቁማል።
- ለመጻሕፍት አዘጋጆች የተሞክሮ ትምህርት ይሰጣል።
- ለሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች መረጃ ይሰጣል።
- ወደፊት ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥ ጥናቶችን ለሚያካሂዱ አጥኚዎች በመነሻነት ያገለግላል ተብሎ ይታመናል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሚሆኑት በ2015 ዓ.ም በአየር ጤና እና በክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መምህራን ናቸው። የዘጠነኛ ክፍል መምህራን እንዲመረጡ የተፈለደገበት ምክንያት የመጻፍ ትምህርትን አስመልክቶ የሚደረጉ ጥናቶች በመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ በርካታ ሥራዎች ቢሠሩ ተማሪዎቹ እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ችሎታቸውን እያሻሻሉ ይሄዳሉ በሚል እምነት ነው። ከይዘት አንደጻር ደግሞ የመምህራኑ ፅህፈት የማስተማር ዘዴ ተግባራትና የማስተማር አቀራረባቸው ተቃኝተው እንዲቀርቡ ከተደረገ በኋላ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ውጤት በንፅፅር የሚፈተሽ ይሆናል።

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ጥናቴ በርካታ ጉዳችን ሊዳስስ ሞክሯል። ነገር ግን በዚህ ጥና ሌሎች ተጨማሪ ት/ቤቶችን ባያካትት ኖሮ የተሻለ መረጃ አግኝቼ ጥናቴ ሙሉ ለሙሉ የተሸለ ይሆን ነበር። ይሁን እንጂ በጥናቴ ውስጥ የንብብ ክሂልን ባካትት ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር። ጥናቴ የተወጣለት ነው ብሎ ለመደምደም አያስደፍርም።

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው መሰረታዊ ጽንሰ ሐሳቦች በዋናነት የመጻፍ ክሂልን የሚደግፉ ንድፈ ሃሳቦች እና ጽሑፍ የማስተማር አቀራረብ ይቀርባል

## 2.1 የጽሁፍ ምንነት

ጽሁፍ አንድ ሰው የራሱን ሃሳብ ለአንባቢ የሚገልጽበት ተግባር ነው፡፡ Bnock (1997)መጻፍ ተራርቀው ለሚኖሩ ሰዎች ሀሳብን በቀላሉ ለመግለጽ አንድን ሀሳብ ለመጪው ትውልድ ለማቆየት ያለፈውን ነገር ለማስታወስ ያስችላል፡፡ ጽሕፈት በተለያዩ ጊዜያት የተከናወኑ ክስተቶችን በቅርስነት በማቆየት ሰዎች የነበረውን ሁኔታ እንዲረዱና እንዲገነዘቡ ያስችላል፡፡ ይህም ጽህፈት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ተሰቶት ተማሪዎች ተምረው እንዲተገብሩትና ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ያስረዳል፡፡

መጻፍ ከቋንቋ መሰረታዊ ክሒሎች ውስጥ አንዱ ነው ፡፡ የተለያዩ ምሁራንም ስለ ክሒሉ ምንነት ልዩ ልዩ ብያኔዎችን ሰንዝረዋል ከነዚህም ውስጥ Raimes (1983) እንደገለጹት መጻፍ በአንባቢ እና በጸሐፊ መካከል ተግባቦት ሒደት ነው፡፡ ይህም ብያኔ የሚያመለክተው አንድ ጸሐፊ የተሰማውን ሀሳብ ስሜት ወይም ፍላጎት በጽሁፍ የሚያሳርፍበት እንዲሁም አንባቢው የቀረበለትን ጽሁፍ ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት እና በንባብ ሂደት ከጸሐፊው ጋር ተግባቦት ለመፍጠር የሚሞክርበት መንገድ ነው፡፡በሌላ በኩል Byrne (1988) መጻፍ ሆሄያትን በወረቀት ላይ ከማስፈር ከፍ ያለ እና በአእምሮ ውስጥ የሚፈልቀውን ሃሳብ በጽሁፍ መልክ ለአንባቢ አቀነባብሮ የመግለጽ ሂደትን የሚያመለክት ነው፡፡

Wallale (2004) በበኩላቸው ጽህፈት ከሰው ልጆች የተግባቦታዊ ሂደት መከወኛ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በቋንቋ ትምህርት ስርአት ትምህርት ውስጥ ተቀርጾ የሚገኝ ነገር ግን በማንኛውም የትምህርት አይነት ውስጥ ጉልህ ፋይዳ ያለው የቋንቋ ክሒል አይነት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ምሁሩ እንደገለጹት ጽህፈት የምንለው የመጨረሻውን ውጤት ሲሆን በውስጥ ግን በአንድ ጊዜ ለመማር ከፍተኛ ተግዳሮቶች ሊኖሩት የሚችልና በርካታ የተነጣጠሉ ንዑሳን ክሂሎች ወይንም ክንዋኔዎች መካከልም ማስታወሻ መያዝ መአከላዊ ጭብጥን መለየት በጋራ መንደፍ ረቂቅ መጻፍና አርትኦት በቀዳሚነት መጥቀስ እንደሚቻል ጠቁመዋል ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎች አንኳር ነጥቦች እንደሚያስገነዝቡት ጽህፈት ከአፍላቂ የክሂል ዘርፎች የሚመደብ ተግባቦታዊ ሂደት እንደሆነ እና በሂደቱም በርካታ የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን የያዘና የአተገባበር ሂደቱም በሰው ልጆች አዕምሮ ውስጥ የሚፈጥረውን ማንኛውንም ረቂቅ ሀሳብ ቅርጽ በመስጠት በገሐድ ይታይ ዘንድ በሆሄያት መሳሪያነት ስምምነት በተደረሰባቸው የአወቃቀር ስርአቶች የሚቀርብ በመሆኑ በትምህርት መታገዝ የሚሻ የክሂል ዘርፍ መሆኑ ነው፡፡

ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን በቅድሚያ ሊያሳካቸው የሚገቡ አላማዎችን ማሰብና መወሰን ይገባል፡፡በመሆኑም በማስተማር ዘዴን በተግባር ላይ ሲውል የምናስተምርበትን ዓላማ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

የጽህፈት ክሂልም ከቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ በመሆኑ የራሱ የሆኑ አላማዎች ይኖሩታል፡፡እንደ Raimes (1983) ገለጻ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ክፍሎች ብዙ የጽህፈት ትምህርት ይሰጣሉ እነዚህ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአረፍተ ነገር አወቃቀር የአገባብና የቃላት ምርጫ ችሎታ ያጠናክሩላቸዋል፡፡ከዚህም አልፎ ከአንባቢ ጋር ለመግባባት ከፊት ለፊት ከሚካሄድ ተግባቦት ውጪ ሃሳብን ለመግለጽ አንድን ጽሁፍ አንብቦ እውቀትን ለማግኘት አንድን የሂወት ተሞክሮ ለቀጣይ ትውልድ መዝግቦ ለማቆየትና በቋንቋው ለተጻፉ የጽሁፍ ስራዎች ተማሪዎች እንግዳ እንዲሆኑ ለማስቻል እገዛ ያደርጋል ፡፡

ይህን ሃሳብ በተመለከተ Attkins (1996) የጽህፈት ክሂል ትምህርት ሁለት አላማዎች እንዳሉት እነዚህም፡-

1ኛ. የተማሪዎች የቋንቋ እውቀት ማለትም የቃላትና የሰዋሰው ችሎታ ማጠናከር ሲሆን

2ኛ. ተማሪዎችተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂልን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ጠቅለል ባለ መልኩ መረዳት የሚቻለው የጽህፈት ትምህርት ዓላማ የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋሰው እውቀትን በማጠናከር በጽሁፍ አማካኝነት መግባባት እንዲቻል ማስቻል ነው፡፡በዚህም ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግር መግለጽ እንደሚችሉ ሁሉ በአዕምሮአቸው የሚመላለሱትን ሃሳቦች በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው መዳበር አለበት፡፡ይህም ከሚያዳምጡት ከሚያነቡት ተነስተው ለግንዛቤ የሚረዳቸውን ሃሳብ መዝግቦ ለመያዝ

ይጠቅማቸዋል። በዚህም ሒደት የቋንቋ ምልክቶችን ከመለየት በተጨማሪ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርአት እንዲያውቁ ያስችላቸዋል።

## 2.1.2 የጽህፈት ትምህርት ባህሪያት

wanger(2002)ለማስረዳት እንደሞከሩት ፤ አንድ ህጻን የተግባቦት ተግባርን የሚጀምረው በአካባቢ የሚገኙ ልዩ ልዩ ድምጾችን በማስቀመጥ ይሆናል።ቀስ በቀስ አስመስሎ ለማጥራት ጥረት ያደርጋል።ለተለያዩ ድምጾች ትርጓሜ መስጠት ይጀምራል ተደጋጋሚ የሆኑ ክንዋኔዎችን በመለየት ለእያንዳንዱ ክስተት ትርጓሜዎችን ወደ መስጠት ይሸጋገራል ። በመቀጠልም እያደገ ሲሄድ ለትርጉሞች የተለያዩ ምልክቶችን ወደ መፈለግና ቀስ በቀስ በወረቀትም ሆነ በሌሎች ነገሮች ላይ የሰፈሩ ምልክቶችን ወይም ቃላት የተለያዩ ትርጓሜዎች እንዳላቸው በማገናዘብ ማንበብ ይጀምራል።ከዚህም በመቀጠል እነዚህን ምልክቶች ወይም ቃላት አመሳስሎ መጻፍ ይጀምራል ይህ ተግባርም አብዛኛውን ጊዜ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በትምህርት የሚገኝ መሆኑን wanger(2002)ያስረዳሉ።የጽህፈት ባህሪያትን በተመለከተ Bumaby(1984)ያቀረቡትን ማብራሪያ ጠቅሰው Nunan(1989)እንደገለጹት ጽህፈት የተለያዩ ሃሳቦችን እያዛመዱ ግጥምጥምነት፤ ውህደትን ወይም አንድነት ያለው መልእክት ማቅረብ የሚጠይቅ ውስብስብ አእምሮአዊ ሂደት በመሆኑ በርካታ ንኡሳን ክሂሎችንና ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚሻ ተግባር ነው።እነዚህ የመጻፍ ክሂልን የተለየ የሚያደርጉትን በርካታ ተግባራት ምንነትና ቅደም ተከተላዊ ሒደቶች በተመለከተም Raimes (1983) እደሚከተለው በዝርዝር አስቀምጠዋል።

- ለምን እንደሚጽፉ ያሳያሉ ይወስናሉ
- ለማን እንደሚጽፉ ወይም የአንባቢያቸውን ማንነት ይለያሉ
- የተለያዩ ተጨባጭ መረጃዎችን በምልክት በማሰላሰል በቃለ መጠይቅ በምክክር
- በንባብ ወዘተ በማሰባሰብ ማስታወሻ ወይም ዝርዝር ሃሳቦችን ይመዘግባሉ።
- መልመጃውን እንዴት እንደሚሰሩት ወይም እንደሚያደራጁት እቅድ ይነድፋሉ።
- የመጀመሪያውን ረቂቅ ይጽፋሉ።
- በረቂቁ ላይ ሂሳዊ ንባብ ያከናውናሉ።
- ጽሁፋቸውን ይከልሳሉ።
- የተሻለ ረቂቅ በማዘጋጀት ከዚያም የመጨረሻውን ቅጂ ይጽፋሉ።
- ስህተቶችን ለመለየት የሚያስችል ጥልቅ ንባብ ያከናውናሉ።

Raimes በተጨማሪ ሲያስረዱ አንድ የጽህፈት መምህር ለተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የጽህፈት መምህር ለተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የጽህፈት ትምህርት ለመስጠት ከመወሰናቸው በፊት

ተማሪዎቹ በጽሁፍ ሂደት የሚያከናዉኗቸውን ዝርዝር ተግባራት መለየትና ማሳወቅ እንደሚገባም ያስረዳሉ፡፡

የጽሀፈት ትምህርት ጠቀሜታ

የጽሀፈት ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ይሀውም የተግባቦት ብቃታቻንን ከፍ በማድረግ ፍላጎታችንን ለማሳካት ያስችለናል፡፡በተጨማሪም ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው Byran (1988) የጽሀፈት ትምህርት ክሂል መዳበር የሚኖሩትን ጠቀሜታዎች በዝርዝር አቅርበዋል እነዚህም ፡-

- ✓ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የመማር ስልት ወይም ፍላጎት እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቋንቋን በንግግር ዘዴ ብቻ በቀላሉ ለመማር የሚቸገሩ አንዳንድ ተማሪዎች በቋንቋው እንዲያነቡና እንዲጽፉ ሲደረግ የበለጠ የደህንነት ስሜት ይፈጥርላቸዋል፡፡እንደነዚህ አይነቶቹ ተማሪዎች ሃሳባቸውን ለብቻቸው ሲገልጹ የበለጠ ነጻ የመሆንና የመዝናናት ስሜትን ሊፈጥርላቸው ስለሚችል ጽሀፈት እንደማነቃቂያ በማገልገል የተነሳሽነት ስሜታቸው እንዲጨምር ያደርጋል ፡፡
- ✓ የቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸው የጽሕፈት ክህሎት መሻሻል ማሳየት አለማሳየቱን ለመረዳት የሚያስችላቸው ተጨባጭ መሳሪያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ፡፡ይሁን እንጂ እውነተኛ የሆነ የችሎታቸው አመልካች ነገር ማለት ባይቻልም ስነልቦናዊ ፍላጎታቸው ማሻሻሉ ሊያመላክት ይችላል፡፡
- ✓ የጽሀፈት ክህሎት መዳበር ከአንድ በላይ መግባቢያ ክህሎት እንዲኖር ያስችላል ፡፡ በተለይም የተለያዩ ክሂሎች በትክክል ከተቀናጀ በአንድ ቋንቋ ብቻ ከሚጠቀሙ ሰዎች የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡
- ✓ የጽሀፈት ክሂል ውስጥ መልመጃዎችን ወይም ተግባራትን የተለያዩ እንዲሆኑ በማድረግ አሰልቺነትን ለማስወገድ ያስችላል፡፡በክፍል ውስጥ የንግግር ልምምድ ሒደት ወቅት ጣልቃ በመግባት የዕረፍት ጊዜ በመሆን ያገለግላል፡፡በዚህም ወቅት ለተማሪዎች ሆነ ለመምህራን የማነቃቂያ ተግባር ሊሆን ይቻላል፡፡በሌላ በኩል ከክፍል ውጪ ባለው የዕለተዕለት ማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚከናወነውን የተግባቦት ሂደት መጠን ያሳድጋል ፡፡
- ✓ ጽሀፈት መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሙከራ ፈተናዎችን ወይም መመዘኛዎችን ለመስጠት ይረዳል፡፡ይህም የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን ይረዳል፡፡

- ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ጠቀሜታዎች እንዳሉትም Raimes (1988) በዝርዝር አቅርበዋል እነዚህም፦

✓ ለተማሪዎች የምናስተምራቸውን የሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን የፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን እንዲሁም የቃላትን ትምህርት ለማማከር ይረዳል፡፡

✓ የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ሲዳብር የተለያዩ ሃላፊነቶችን በመረከብ በቋንቋው የሚኖራቸውን ተጠቃሚነት ያሳድገዋል፡፡

✓ የጽህፈት ክሂል ሲዳብር ብዕርና ወረቀትን በማገናኘት ሃሳባቸውን ለመግለጽ በሚያደርጉት ያላሳለሰ ጥረት አዳዲስ ቃላትን የመጠቀም አዲስ ሃሳብ የማመንጨትና ሃሳቦችን በተለየ መልኩ በብቃት የመግለጽን ልምምድ እንዲያዳብሩ ይረዳል በማለት ያስረዳሉ፡፡

## 2.1.3 የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

የጽህፈት ትምህርትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እንዳሉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ እንደ Barbara (1997) ገለጻ ጽህፈት ባሉት ባህሪያት የተነሳ ውስብስብና በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊዳብር የሚችል ክሂል ባለመሆኑ ብዙ ጊዜ ወስዶ ልምምድ ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡በባህርይው የተለያዩ ክሂሎችን የሚጠይቅ በመሆኑ አፋቸውን በቋንቋው ለፈቱትም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት ተማሪዎች ለሁለቱም በእኩል ደረጃ አስቸጋሪ እንደሆነ kyoll (1990) ያስረዳሉ፡፡ሌሎች ጽህፈትን አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉት ባህሪያቱ ደግሞ ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና አዕምሮአዊ ገጽታዎች ናቸው እነዚህን ባህሪያት በተመለከተ ምሁራን የሰጡትን ሀሳብ እንመለከታለን፡፡

### 2.1.3.1 ስነ ልቦናዊ ባህርይ

በጽህፈት ክሂል የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚጻፈውን ጽሁፍ ለማን እንደሆነ ወይም አንባቢውን ማሰብ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡መልእክቱ ለአንባቢው በትክክል እንዲደርሰው ለማድረግ ደግሞ ጸሃፊው በሃሳብ መውጣት መውረድ ስላለበት ይጨነቃል የጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና መተንፈሻ እግራቸውን ማፋተጊያና እርሳሳቸውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው፡፡በማለት ጽህፈት ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ Hedge (1983) ይገልጻሉ ከዚህ ሃሳብ በመነሳትም የጽህፈት ክሂል ውስጣዊ ጭንቀት የሚፈጥርስነልቦናዊ ችግር መሆኑነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.1.3.2 ስነ ልሳናዊ ባህርይ

ስነልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድን ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታው ይጠናበታል፡፡በጽህፈት ትምህርት ረገድም የስነልሳን እውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ሀሳብን በጽህፈት አማካኝነት በትክክል መግለጽ የሚቻለው የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ተቀባይነትና ተነባቢነት ያለው መልዕክት ለማስተላለፍ የግድ የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ተቀባይነትና ተነባቢነት ያለው መልዕክት ለማስተላለፍ የግድ የቋንቋውን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ይህ ደግሞ የቋንቋውን ስርዓት ከአጠቃቀሙ ጋር አስማማምቶ በማቅረብ በጽሁፍ መግባባት ያስችላል፡፡ይህን እውቀት ለማዳበርም በንግግር ወቅት ትኩረት የማናደርግባቸው ነገር ግን በጽህፈት ጊዜ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነገሮች መኖራቸውን መፈተሻ ይገባል Hedge(1988) በማለት ያብራራሉ፡፡እላይ የቀረበውን የምሁሩን ሀሳብ ስንመለከት ስነ ልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታው የሚጠናበት በጽሕፈት ትምህርት ረገድም የስነ ልሳን እውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን የቀረቡት ገለጻዎች ያስረዳሉ፡፡

## 2.1.3.3 አእምሮአዊ ባህርይ

ጽህፈት በከፍተኛ ደረጃ የአእምሮ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ትምህርት ነው፡፡የጽሁፍ ስራ የግንዛቤን መዳበር ይጠይቃል፡፡ Moore (1995:13)" መጻፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው፡፡" ሳይታሰብበት የሚከናወን የጽህፈት ተግባር አለመኖሩን ይገልጻሉ ፡፡ Reid (1993) በበኩላቸው የጽህፈት ትምህርት እጅን አይንንና አእምሮን በማስተባበር በተገቢ ትዕምርታዊ ወኪሎች አማካኝነት የራስን ወይም የጋራን ገጠመኝ የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡በማለት አእምሮ ለጽህፈት ትምህርት ክንውን ያለውን አስተዋፅኦ በአፅዕኖት ገልጸዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደሞከርነው የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች በመነሳት ክሂሉን ለማስተማር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን የሚጠይቁ ነገሮች እንዳሉ መገንዘብ ይችላል፡፡ከዚህም በመነሳት የተማሪዎች የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነገሮችን ጠንቅቆ በመለየት ማስተማር እንደሚገባም ከላይ በዝርዝር የቀረበው የምሁራን ሃሳብ ያስረዳናል፡፡

## 2.2 የጽህፈት የማቀድና ማስተማር መርሆዎች

ጽህፈትን በማስተማር ሂደት ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት ሃሳባቸውን በተገቢው ሁኔታ የመግለጽ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ መምህሩ የጽህፈትን ክሂል በሚያዳብሩና የጽሕፈት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህርቱን ማቅረብ እንዳለበትና በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆዎች ማስታወስ ተገቢ እንደሚሆን Atkins (1996) ይገልጻሉ፡፡እነዚህም መርሆዎች ፡-

- ✓ የመጻፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የሚለማመዱት መሆን አለበት፡፡ በክፍል ውስጥ የሚለማመዱት መሆን አለበት ፡፡በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለጊዜ ለሰዋሰውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት የመጻፍ ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መልመጃዎችም አስደሳችና ለመጻፍ የሚያነሳሱ ዓላማ ያላቸው የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃ እና ልምዳቸውን ያገናዘበ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ የሚያስችል ለውይይትና ለቡድን ለመጻፍ ተስማሚ የሆነ ግልጽ መመሪያዎች ያሉትና ተማሪዎች እንደያቅዱ እንዲያረቁና እንዲከልሱ የሚያበረታታ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡
- ✓ ተማሪዎች እንዲጽፉ ከመናገራቸው በፊት ተማሪዎችን ማነሳሳት፡፡
- ✓ ተማሪዎች በግል በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሰሩ ከተፈለገ በቅድሚያ በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል፡፡
- ✓ መልመጃዎች ሲከናወኑ መቆጣጠር በቁጥጥር ወቅት ጠቃሚና ገንቢ ምላሽ መስጠት በዚህም ከፍተኛ ጥር በማድረግ ላይ ያሉትን በመለየት ድጋፍ መስጠት ማድነቅና ማበረታታት ጽሁፋቸውን ማረም አስተያየት መስጠት ተማሪዎች መጻፍ የሚፈልጉባቸውን ሃሳቦች በመቀበል በተቻለ መጠን ግልጽ እና ትክክል በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት፡፡
- ✓ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ከተፈላጊው ደረጃ ላይ ከደረሰ ተማሪዎችን ሊፈትኑ የሚችሉ አዝናኝና ልቅ የያልሆኑ ውስን መልመጃዎችን ማቅረብ፡፡
- ✓ ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው እንዲጻጻፉ ማበረታታት፡፡የጻፉትን ጽሁፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጣጡ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ እላይ የቀበውን የምሁራን ሀሳብ ስንመለከት የጽሕፈት ማቀድ እና ማስተማር መርሆዎች ጽሕፈትን በማስተማር ሒደት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲያሳድጉ የጽሕፈት ክሒላቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ መርሆዎች መሆናቸውን ከቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.3 የጽህፈት ክሂል ትምህርት ማስተማሪያ አቀራረቦች

የጽህፈት ትምህርትን ለማስተማር ወጥ እና ቀላል መንገድ ባይኖርም የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል Ramies (1983) ያስረዳሉ፡፡እኚሁ ምሁርም አያይዘው ሲገልጹም ከተገደበ የጽህፈት አጻጻፍ አንስቶ በቅርብ ጊዜ እየተለመደ ወዳለው ሂደታዊ አቀራረብ ድረስ የተለያዩ የጽህፈት ማስተማሪያ መንገዶች በስራ ላይ የዋሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት ቢያዳግትም ከጥናቱ ርእስ አኳያ ተዛማጅነት ያላቸውን በአንጻራዊነትም ሲቃኙ የቅርብ ጊዜያት አቀራረቦች ሊባሉ የሚችሉና በተለያየ ምሁራን Yan (2005) Lim (2007) Ferris (2003) በተደጋጋሚ የተጠቀሱትን አራት አቀራረቦች ማለትም ውጤት ተኮር፣ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ፣ ጀነር አቀራረብነ እና ሂደት ወጀነር አቀራረቦችን ምንነትና የአተገባበር ሂደታቸውን እንዲሁም ጥንካሬዎቻቸውንና ያለባቸውን አጥርቶች በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡትን አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.3.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ

ይህ የጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ከሶስቱ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች ቀዳሚ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው Kaplan(1967) ኮንትራስቲብ ሪቶሪክ በሚል ርእስ ባቀረቡት መጽሃፍ ውስጥ ነው፡፡በውጤት ተኮር አቀራረብ መምህራን ትኩረት የሚያደርጉት ስህተት የሌለውና ግጥምጥምነት አለው ተብሎ የሚታሰበው በተማሪዎች የመጨረሻ ጽሁፋዊ ስራ ላይ እንደሆነ Nunan(1989) ያስረዳሉ፡፡ውጤት ተኮር አቀራረብ በJohns(1986) ገለጻ መሰረትም የበለጠ ጠቀሜታ የሚኖረው በጽሁፍ የመጀመሪያ እርከን እና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ ለተገኙ ተማሪዎች ነው ተብሎ ቢታመንም ይህ ስነ ትምህርታዊ አቀራረብ ሌሎች ጸሃፊያንም ሃሳባቸውን ውጤታማ በሆነ ስልት እንዲያደራጁ ሊረዳቸው እንደሚችል ጠቁመዋል ጸሃፊው እንደገለጹት በአንጻሩ ይህ ዘዴ የራሱ የሆኑ የታወቁ ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ የጽህፈት ትምህርት ላይ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂል ከማጎልበት አኳያ የተወሰኑ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡ውጤት ተኮር አቀራረብ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚኖረው

ጠቀሜታ ተማሪዎቹ ከቀረበላቸው ሞዴል ጽሁፋዊ ስራ ላይ ሀይለቃልን የመሸጋገሪያ ቃላትንና ሀረጋትን የአንቀጽ አገነባብ ስልትን የሀሳብ አሰዳደር ስርአትንና በአጠቃላይም የአጻጻፍ ብልሃት አተገባበር ስልትን በምሳሌዎች እንዲረዱ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡

ውጤት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ሶስት የተለያዩ ደረጃዎች አሉት፡፡እነዚህም፡- ውስን ጽህፈት፣ መር-ጽህፈት እና ነጻ-ጽህፈት መሆናቸውን Richards (1990) ጠቁመው ምንነታቸውንና የአተገባበር ሂደታቸውን በተመለከተም በስፋት አብራርተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተለያዩ ምሁራን ካቀረቡት ባብራሪያ መረዳት የሚቻለው ውጤት ተኮር ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ እና ለጀማሪ ምሁራን ሞዴል ጽሁፋዊ ስራዎችን በማቅረብ፣ ሃሳባቸውን እንዴት አደራጅተው እንደሚያቀርቡ በመነሻነት ቢያገለግላቸውም፣ በሌላ በኩል ግን ችግሮችበን ያለበት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከከነዚህ ችግሮች ውስጥ ቀዳማዊ የሆነ መምህሩን የሚያቀርቡበት ጽሁፋዊም ሆነ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አለመኖር ወይም ምጋቤ ምላሾቹ የሚቀርቡት በተማሪዎች የመጨረሻ ፅሁፍ ላይ በመሆኑ ምክንያት የተማሪዎች የተሰጧቸው የመምህር አስተያየጦች ተግባራዉ በማድረግ ፅሁፋዊ ስራዎቻቸውንም ሆነ የመጻፍ ክሂላቸውን የማሻሻል እድል እየሰጣቸውም ከዚህ ምክንያት በርካታ የተቃውሞ ሃሳቦችን ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡

በውጤት -ተኮር አቀራረብ ስርዓት የተለመደው የአጻጻፍ ሂደት በቨመጀመሪያ መምህራን የመጽሁፍን ርዕስ በመወሰን ተማሪዎች እንዲጽፉ ካደረጉ በኃላ ስራዎቻቸውን በመሰብሰብ ምንም አይነት ምልክት፣ እርማት ወይም ማሻሻያ ሃሳብ ሳያቀርቡ ለተማሪዎቹ ስለሚመልሱ፣ ተማሪዎቹ ማሻሻያ እንዲያከናወኑ የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ እነዚህ የመቃወሚያ ሃሳቦች ቢቀርቡበትም በዚህ አቀራረብ መሰረት የተማሪዎች የመጨረሻ ፅሁፋዊ ስራ ከሆሄያት፣ ስርዓተ ነጥብ እና ሰዋሰዋዊ ግድፈቶች የጸዳ የሆነ እንዲሆን ስለሚፈልግ እስካሁን ድረስ የተወሰነ ተቀባይነት ሊያገኝ መቻሉን Yan (2005) ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ ይህ አቀራረብ ባቀረቡበት ሂሣዊ አስተያየቶች ምክንያት ምሁራን ችግሮችን ሊቀርፉ ይችላል ብለው ያሰቡትን ተከታዩን የፅህፈት ማስተማሪያ አቀራረብ በአማራጭነት አቅርበዋል፡፡

## 2.3.2 ሒደት -ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር በነበሩበት ክፍተቶች ምክንያት ወደ ተለዋዋጭ (daynamic)፣ ኢ-መስመራዊ (non-daymanic ) እና ድግግሞሻዊ ሂደትን (recurecive procesess ወደ ሚከተለው ሂደት ተኮር ማስተማሪያ ስነ ዘዴ መቀየሩን Jordan (1997) ጠቁመዋል፡፡

ሂደታዊ አቀራረብ መደበኛ ሞዴሎችን የሚከተል ሳይሆን ጸሀፊው በሚጽፍበት ጊዜ ምን ማከናወን እንሚኖርበት አቅጣጫዎችን አመላካች ነው፡፡ ውጤት ተኮር አቀራረብ የመጨረሻው ነው ተብሎ የሚታሰብ የተማሪዎች ስራ ሊያተኩር በአንጻሩ ሂደት ተኮር አቀራረብ የመጨረሻው ፅሁፋዊ ስለበሚያስገኘው ፅሁፋዊ ሂደት ላይ የሂደታዊ አቀራረብ የመጨረሻ ፍፁም ትክክለኛ ፅሁፍ ሊኖር አይችልም፡፡ የሚለውን ሃሳብ ቢከተል ማንኛውም ፅሁፍ ከቅድመ ፅህፈት ተግባር ጀምሮ በምክክር፣ በክለሳ፣ በእርማትና ረቂቁን መልሶ በመጻፍ ወደ ትክክለኛነት ማምጣት ይቻላል የሚል አስተያየት ይከተላል።

## 2.3.3 ጃነር ጽኅፈት ማስተማሪያ አቀራረብ

በ1980ዎቹ ታዋቂነትን እያገኘ የመጣው ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የተለያየ የአፃፃፍ ስልቶች ማስተማሪያ የበለጠ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላል ከሚለው አስተያይ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶችን እያጠኑ ሲሄዱ በተጓዳኝነትም የተለያዩ መዋቅራዊና ቅርጻዊ የአጻጻፍ ስልቶችን በመረዳት በፅሁፋዊ ስራዎቻቸው ውስጥ የተማሯቸውን የአጻጻፍ ስልቶች ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ አቀራረብ፣ አካዳሚያዊ ፅሁፎች በሚዛወተሩባቸው በክፍል ውስጥ ፅሁፋዊ ልምምዶች ላይ፣ መምህራን በገሀዱ አለም ውስጥ የሚተገበሩትን ልዩ ልዩ የፁሁፍ ኤነቶች በክፍል ውስጥ በመልመጃነት እንዲለማመዱ የሚያበረረታታ የአጻጻፍ ዘዴ በመሆኑ በመጠቀም (Yan 2005) ሦስት አበይት ደረጃዎችን ተከትለው ስነ ፅሁፋዊ ስራዎች ይዘጋጃሉ በማለት ያቀርባሉ፡፡ እነዚህም፡-

1. የታቀደውን የፅሁፍ አይነት በሚያስገነዝብ ማሳያ ሞዴል ለተማሪዎች ቀርባል፡፡
2. የፅሁፋዊ ስራው ጀምሮ በመምህርና በተማሪዎች ትብብር ይገነባል፡፡
3. የመጀመሪያው ረቂቃዊ ፅሁፍ በእያንዳንዱ ተማሪ በግል ይከናወናል፡፡

ይህ አቀራረበን ጽህፈት በማህበራዊ አውድ ውስጥ ይከናወናል የሚለውን ሃሳብ ያዳብራል፡፡ በተጨማሪም የተወሰነ አላማም ይንፀባረቅበታል፡፡ ይህም ዓላማ መማር እንዲኖር የሚችለው በሙሉ ንቃት እና ህሊና በሚከናወን ማስመሰል እና ትንታኔ ነው የሚል ሲሆን ግልጽ የሆነ የማስተማር ሂደትን ያመቻቻል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ የመቃወሚያ ሃሳቦች ውስጥ ቀዳማዊ ፅሁፋዊ ስራን ለማከናወን አስፈላጊ ለሆኑት ሂደታዊ ተግባራት ዝቅተኛ ትከረት መስጠቱ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎችን እጅግ ደካማ አድርጎ መመልከቱ ሌላው ደካማ ጎን ነው፡፡ badger (2000) እነዚህ ከላይ የቀረቡት የተለያዩ የፅህፈት ማስተማሪያ አቀራረቦች የየራሳቸው የሆኑ ጥንካሬዎች ቢኖራቸውም በአንጻሩ ድክመትም እንዳለባቸውም በተለያዩ

ምሁራን Broown (1994)፣ Badger (2000)፣ Yan( 2005)፣ …ተጠያቃዊ በሆኑ ማስረጃዎች በመገልጽ ምክንያት፣ ምሁራን ከአንድ በላይ የፅህፈት ማስተማሪያ አቀራረቦችን በማቀናጀት ተከታየን የፅህፈት ማስተማሪያ አቀራረብ በአማራጭነት ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡

## 2.3.4 ሒደት ወ ጀነር ጽህፈት ማስተማሪያ አቀራረብ

በአሁኑ ጊዜ በበርካታ የፅሁፍ መምህራን ተቀባይነት ያለው የፅህፈት ማስተማሪያ አቀራረብ ነው፡፡ በመማሪ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ አንድ አይነት የፅሁፍ ማስተማሪያ አቀራረብን ከመጠቀም ይልቅ፣ ከተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች ውስጥ ተመራጭ የሆኑ ገፅታዎች መርጦ በማዋሀድ መጠቀሙ አዲስ ግኝት እየሆነ መምጣቱን Yan (2005) ጠቁመው ለዚህ ተግባር አንዱ ምሳሌ ከሂደታዊ አቀራረብ እና ከጀነር አቀራረብ ውህደት የተገኘ Badger & White (2000) ሒደት ወጀነር አቀራረብ በማለት የሰየሙት አቀራረብ ስልት መሆኑን Yan (2005) አስረድተዋል፡፡

ሂደት ወጀነር አቀራረብ ስድስት የተለያዩ ደረጃዎችን ወይም ቅድመ ተከተላዊ የማስተማር ሂደት ደረጃዎችን ይከተላል፡፡ እነዚህም 1 ዝግጅት 2፣ ሞዴል ማጠናከር፣ 3. ማቀድ፣ 4 በጋራ መስራት ፣ 5 በግል መስራት፣ 6 መከለስ ናቸው፡፡ yan 2000)

እነዚህ ስድስተር ደረጃዎች ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸውን ተግባራት በመሆናቸው ምክንያት ግልጽ የሆነ ድንበር መፍጠር ባይቻልም በተናጠል ሲታዩም ግን ማን ማለት እንደሆኑ yan (2005) እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል፡፡

1. ዝግጅት፡- መምህሩ ተማሪዎቹ ለፅህፈት እንዲዘጋጁ ለማድረግ ይቻላቸው ዘንድ በአንድ የአጻጻፍ አይነት ለምሳሌው በአማዛዛኝ አከራካሪ ፅሁፍ ሊቀርብ የሚችል ወቅታዊ አነጋጋሪ ሁኔታ በማንሳትና አስፈላጊ ገለፃ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማነሳሳት ይቻላል፡፡
2. ሞዴል መፍጠርና ማጠናከር፡- መምህሩ የተመረጠውን የፅሁፍ አይነት በማስተዋወቅ ተማሪዎቹ አንባቢያቸውን ማንነትና የሚኖረውን ማህበራዊ ፋይዳ እንዲያገናዝቡ መፍቀድ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የፅሁፍ አይነት አመዛዛኝ ፅሁፍ ከሆነ ዓላማው ሊሆን የሚችለው አንባቢያን በማሳመን አንድ ድግሪት እንዲከናወን ማድረግ ነው፡፡ በመቀጠልም መምህሩ ፅሁፍን እንዴት በማዋቀርና በማደራጀት ዓላማውን ማሳካት እንደሚቻል ምክክር ወይም ገለፃ ያከናውናሉ፡፡ ተማሪዎችም የተማሩትን የፅህፈት

3. ዓይነት ለማጠናከር ይችሉ ዘንድ ምክክሩን ወይም ገለፃውን ከአንድ ፅሁፍ ጋር ሊያነፃፅሩት ይችላሉ፡፡
4. ማቀድ፡- በዚህ ደረጃ በርዕሱ ጉዳይ ላይ የተማሪዎች ምናብ ወይም ግንዛቤ የሚያዳብሩ በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል ማሰላሰል፣ መወያየት እና ተዛማጅ ፅሁፎችን ማንበብ ይጠቀሳሉ፡፡ የተግባራቱ መሰረታዊ ዓላማም ርዕስ ጉዳዩን ከተማሪዎቹ ቀደምት ልምድ እና ግንዛቤ ጋር በማስተሳሰር የተነሳሱት ስሜታቸውን ማጎልበት ነው፡፡
5. በጋራ መስራት፡- በዚህ ደረጃ ግላዊ ፅህፈት ትግበራ ሂደት የሚያመቻች ሲሆን ፅሁፋዊ ስራውን ለመጀመር ይቻል ዘንድም መምህሩ እና ተማሪዎች በጋራ ይሰራሉ፡፡ ስለዚህም የማሰላሰል፣ የማርቀቅና የመከለስ ፅሁፋዊ ሂደቶች በትብብር ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ መረጃዎችን ና ሃሳቦችን በማቅረብ ሲሳተፉ፣ በተመሳሳይ መምህሩም በተማሪዎቹ የቀረቡትን ሃሳቦችና መረጃዎች በማደራጀት በጥቁር ሰሌዳ ወይም በኮምፑተር ላይ ይፅፉሉ፡፡ በዚህ መልክ በቅንጅት የተገነባ ፅሁፋዊ ስራ የመጨረሻ ረቂቅም ተማሪዎቹ ግላዊ ፅሁፋቸውን ሲያዋቅሩ እንዲያገለግሉበት በሞዴልነት ይቀርባል፡፡
6. በግል መስራት፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በቀረበላቸው ሞዴል ላይ ተመስርተው ተመሳሳይ በሆነ ርዕስ ጉዳይ ላይ ግላዊ ስራቸውን የሚያከናውኑበት ነው፡፡ ይግን ተግባር ለማከናወን የተመደበውን የትምህርት ክፍለ ጊዜም በቂ ላይሆን ስለሚችል አተገባበር ሂደቱን በተመለከተ መምህሩ እገዛ፣ ገለፃና ምክር ሳይለያቸው ስራውን በክፍል ስራ፣ በቤት ስራ ወይም በተመሳሳጥ መልክ ሊያከናውኑት ይችላሉ፡፡
7. መከለስ፡- ተማሪዎቹን የመጀመሪያውን ረቂቅ ካጠናቀቁ በኃላ የመምህራቸውን ተግባር የሚሆነው የተማሪዎቹን ስራ አንድ በአንድ በመሰብሰብ ውጤት/ማርክ መስጠት ሳይሆን በድጋሚ በሚሰጧቸው መመሪየቀዎች እየታገዙ ስራዎቻቸውን በማረም፣ በመገምገም፣ ወዘተ… የማሻሻል ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡

## 2.4. በፅህፈት ትምህርት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ

Hayland (2000) ፣ chane (1990) ፣ Bitchener 2005) የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሂደትና አይነቶችን ግምገማ፣ የጓደኛ ምጋቤ ምላሽ፣ የመምህር ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ እና የመምህር ተማሪ ምክክራዊ ምጋቤ ምላሽ አይነት በማለት ምንነትና አተገባበርቸው እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

### 2.4.1. የግል ግምገማ

የግል ግምገማ የሚከናወነው በፀሀፊው በራሱ በተማሪው አማካኝነት ነው፡፡ መሰረታዊ ዓላማውም ተማሪዎች በፅሁፎቻቸው ላይ ተደጋጋሚ ሒሳዊ ንባብ በማከናወን የሃሳባቸውን ትክክለኛነት. ተጠያቂነት፣ ተያያዥነት፣ ወዘተ.... በመመርመር ክለሳ በማድረግ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ ማስቻል ነው፡፡ የግል ግምገማ ያከናወኑት ተማሪዎች ጓደኛ ምጋቤ ምላሽ ከተቀበሉት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የመጻፍ ክሂል መሻሻል ማሳየታቸውንም Oslon (1990) አስረድተዋል፡፡

በጽሕፈተት ትምህርት መጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የግል ግምገማ አስፈላጊ እንደሆነና የጓደኛ ምጋቤ ምላሽን አስፈላጊነትን በመግለጽ የግል ግምገማ ከጓደኛ ምጋቤ ምላሽ የተሸለ መሆኑን ከቀረበው የምሁራን ማብራሪያ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.4.2. ጓደኛ ምጋቤ ምላሽ

የጓደኛ ምጋቤ ምላሽ አንድ መሰረታዊ የመማር ማስተማሪያ ተግባር አካል ሲሆን ተማሪዎች የየራሳቸው የሆኑ አድማጮች እንዷላቸው እንዲያስቡና የተነሳሽነት ስሜታቸው እንዲጨምር እገዛ ያደርጋል፡፡ Mogahed (2009) በተጨማሪም ጓደኛ ምጋቤ ምላሽ ፈጠን ምጋቤ ምላሽ በማስገኘቱ የመምህሩንና የተማሪዎችን ጊዜ ቆጣቢ ከመሆኑ ዘንጻር ተመራጭነት እንዳለው Kech (1990) ጠቁመዋል፡፡

### 2.4.3. የመምህር ምጋቤ ምላሽ

የመምህር ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች የፅህፈት ስራ ላይ የሚቀርብን ማንኛውንም ግብዓት ያካትታል፡፡ ህ ምጋቤ ምላሽ ተዘውታሪና ተማሪዎች ፅህፈት ስራዎቻቸውን ለመከለስ የሚያስችሏቸው የምጋቤ ምላሽ ምንጭ ነው፡፡ እንደ Edg 1990) ገለፃ የመምህር ምጋቤ ምላሽ ዓላማ በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ የሚገኙትን ችግሮችን በማረም ፍፁም ትክክለኛ ስራ ማድረግ ሳይሆን ተማሪዎች ማስተላለፍ የፈለጉትን ሃሳቡን የሚገልፁትን ስልት እንዲማሩ መረዳት ነው፡:

### 2.4.4. የመምህር ተማሪ ምክክር ምጋቤ ምላሽ

የመምህር ተማሪ ምክክርና ተማሪዎች ፊት ለፊት በመገናኘት በተማሪዎች ፅሁፋዊ ስራዎች ላይ ምክክር በማካሄድ፣ ለፅሁፋዊ ስራው ማሻሻልና ለማጻፍ ክሂል ማዳበር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚለዋወጡበት ሂደት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የመምህር ተማሪ ምክክር ፅህፈትን ከማስተማር አንጻር ትክለኛ መምህርና የተማሪ መስተጋብር የሚከናወንበት አውድ መሆኑን Regested 91980) ያስረዳሉ፡፡በመምህር ተማሪ ምክክር ሂደት የመምህሩ ሚና

የተማሪዎችን አስተሳሰብ ሊያሰፉ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ አሰተያየጦችን ማቅረብ፣ አስተሳሰባቸውን የሚፈታተኑ አዳዲስ ሃሳቦችን ማስተዋወቅ ወይም ለአዕምሮአቸው ተጫመሪ ምግብ ማቅረን መሆኑን Keebler 1995) ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለመመልከት እንደሚቻለው በጽሕፈት ትምህርት ምጋቤ ምላሽ አሰጣት ሒደት የተጠቀሱት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አይነቶች ለጽሕፈት ትምህርት አስፈላጊ መሆናውን ከቀረበው ገለጻ ለመረዳት ይቻላል፡፡

## 2.5. የመጻፍ ክሂል ምዘና

በፅህፈት ምዘና ላይ ቀዳሚው ሊሰጣቸው ከሚገቡ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ተገቢነት ያለው የመመዘበኛ መስፈርት መምረጥና የፈተናውን ዓላማ መሰረት ያደረገ መስፈረት መወሰን ነው፡፡ Bacha (2001) ከዚህ አኳያ ሆልስቲክ እና እናሊስቲክ መመዘኛ መስፈርቶች መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችሎታ እንዲያዩ የሚያስችሏቸውና አስተማማኝነት እና ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውም በበርካታ ጥናቶች የተረጋገጠ መሆኑን Bacha 2001) አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ ሁለት አይነት የተማሪዎች ፅህፈት መመዘኛ መስፈርቶች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን Bacha (2001)፣Izadpanah (2004) ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ የመመዘኛ መንገዶች ሆልስቲክ መሰፈርት እና አናሊስቲክ መስፈርት መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ ምንነታቸውና አተገባበራቸውም በቀጣይ ያቀርባል፡፡

### 2.5.1. ሆልስቲክ መመዘኛ መስፈርት

በአሁኑ ጊዜ በተግባር ላይ የተማሪዎችን ፅሁፋዊ ስራ ለመመዘን ከሚያስችሉ መስፈርቶች መካከል አንዱ ሆልስቲክ ነው፡፡ ዓላማው የቀረበውን የተማሪዎች ፅሁፋዊ ስራዎች አጠቃላይ የሆነ ችሎታ በመገምገም ነው፡፡ በዚህ መመዘና መስፈርት የተማሪዎች ፅህፈት የትኞቹ ጉዳዮች ላይ ችግሮች እንዳሉባቸው ከማመልከት ይልቅ ተማሪዎቹ በተሻለ ሁኔታ ያከናወኗቸውን ጉዳዮች የሚገልጽ ናቸው ብለው Wisman (2012) ባቀረቡት ትናታዊ ስራ አመላክተዋል፡፡ ይህ የምዘና መስፈርት ከሌሎች የምዘና መስፈርቶች የሚለይበት አይነተኛ ባህሪውም ስለተማሪዎቹ ፅሁፋዊ ስራዎች የክሂል ማሻሻል ወይም መቀነስ አጠቃላይ የሆነ መረጃን የሚሰጥ እንጂ ለውጡ የታየው፣ በየትኛው ንዑስ ክሂል ላይ እንደሆነ በግልጽ አውጥቶ አያመለክትም፡፡ ይህ መመዘኛ መስፈርት ጊዜ ቆጣቢ ነው አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ የሚደረገውም በርካታ ተማሪዎች በሚገኙበት ክፍል ነው፡፡ በማለት አያይዘው Wisman (2012) ያስረዳሉ፡፡

## 2.5.2. አናላይቲክ መመዘኛ መስፈርት

ይህ የመመዘና መስፈረት የተማሪዎችን የፅሁፍ ስራ ለውጤት አሰጣጥ ሂደቱ የበለጠ የተመቻቸ ይሆን ዘንድ አንድን ፅሁፋዊ ስራ የተለያዩ ንዑሳን ገፅታዎች በሚያሳይ መልኩ ፅሁፋዊ ስራውን ወደ ንዑሳን ምድቦች ከፋፍሎ የሚታኝ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ፅሁፋዊ ስራዎች ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት ከቋንቋ አጠቃቀም ወይም ከስርዓተ ፅህፈት አኳያ በመገምገም የሚያቀርብ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ስፀሀፊው ብቃት በመመርመር ጥልቅ ሆነ ዝርዝር መረጃዎችን ከተለያየ የአንግሎች አንጻር ሊያሳይ ይችላል፡፡ Kuo (2007) ይህ መመዘኛ መስፈረት የተማሪውን ፅሁፍ መርምሮ ጥልቅ የሆነ ዝርዝር ጠቃሚ በተናጠል ለማሳየት የሚያስችል እንደሆነም Cohen (1994) ያስረዳሉ፡፡

## 2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የምንመለከተው ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን ቀደምት ስራዎች ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ከዚህ ቀደም ከቀረቡት የሌሎች አጥኚዎች ስራ ጋር ሚያመሳስልበትና የሚለይበት ሁኔታ በቀጣይ እንመለከታለን፡፡

ማረው (1987) ‹‹ በግልና በቡድን የሚጻፍ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ በኢትዮፕያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ በሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ የደረሱበት መደምደሚያ በግል ከሚጻፍ ድርሰቶች ይልቅ በቡድን የሚጻፉት የተሻሉ መሆናቸውን በግል ድርሰትና በቡድን ስራ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩንና የቡድን ስራ ለድረሰት ትምህርት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን አመልክተዋል፡፡

እንዳለ (1992) በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ‹‹ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቢ ሚና›› በሚል ርዕስ ያከናወኑት ጥናት ዓብይ አላማ መምህሩ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት መጻፍ ችሎታ ላይ መሻሻልን ያስከትላልን? የሚለውን ጥያቄ መመርመር ነው፡፡ ትናቱ አይነታዊ የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሂደትን ተግባራዊ በማድረግ የተከናወነ ሲሆን፣ የመረጃ ትንተናው ተካሂዷል በተገኘው ውጤት መሰረትም ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የድርሰት ችሎታ እንደሚያሻሽል መረጋገጡን አጥኚው ጠቁመዋል፡፡ በመጨረሻ ላይ አጥኚው በሰጡት አስተያየት፣ “ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በየጊዜው በድርሰት መስክ በመካሄዱ ምርምሮች መታነጽ አለበት፡፡” በማት ጠቁመዋል፡፡

ሰለሞን (1987) በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ‹‹ የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት ‹‹ በሚል ርዕስ ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡ የዚሁ ጥናት ዓበይ አላማ ተማሪዎች የብጤ እርማትን እንዲጠቀሙበት ቢደረግ ተግባራዊነቱን

እንደሚመስል አመልክቶ የሚያስገኘውን ውጤት መግለፅና ማብራራት ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው በርካታ ተማሪዎች በሚገኙበት ክፍል ውስጥ ይህን የብጤ እርማት ለመተግበር መቻሉን ነገር ግን ተማሪዎችን አሁን ባሉበት ወቅት በልምድ ማነስ ምክንያት በተሟላ መልኩ ምጋቤ ምላሽ መስጠትም ሆነ መቀበል አለመቻላቸውን ነው፡፡ ከጥናቱ በመነሳትም አጥኚው በሰጡት አስተያየት የብጤ እርማትን አሰራር በሙከራ ስለማሻሻል፣ የአሰራሩን ውጤታማነት በተራዘመ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለመፈተሽ ተገቢነት መስጠት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለፁት ጥናታዊ ስራዎች ከዚህ ጥንታዊ ስራ ጋር ያላቸውን ዝምድና ማዕከላዊ ጉዳዮቻቸውን በፅህፈት ትምህርት የመምህራኑ ሚና፣ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖርም፣ በአንጻሩ ግን የጥናቶቹን አቅጣጫ ስንመለከት ግን ከዚህ ጥንታዊ ስራ ርዕስ ጋር ሰፊ ልዩነት አሏቸው፡ ፡ በቅድመ ተከተል ስንመለስት የእንዳለ (1992) ጥናቱን ስንመለከት በመምህራን ምጋቤ ምላሽ እና በማተኮር፣ አይነታዊ የአጠናን ዘዴ በመከተል የመምህር ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ እና የመምህር ተማሪ ምክክራዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ፅሁፋዊ ስራዎች እድገት ላይ የሚኖራቸውን በማድረግ ተከናውኗል፡፡ በተማሳሳይ ሰለሞን (1987) የተከናወነው በቢጤ እርማት ውጤታማነት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ጥናት ትኩረቱን በመምህር ምጋቤ ምላሽ ላይ ያደረገ በመሆኑ በቀዳሚነት የጎላ ልዩነት አለው፡፡

በጠቃላይ የማረው፣ እንዳለ እና ሰለሞን ስራዎች በፅህፈት ስራ ላየጥ የቀረቡ በመሆናቸው በጥናት ዘዴም በመጠኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ ቢሆንም ትኩረታቸውና ዓላማቸው በተማሪ በሚጻፍ ድርሰቶችን፣ በመምህራን ምጋቤ ምላሽ እና የቢጤ እርማት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የዚህ ጥናት አብይት ትኩረትና አላማ ግን በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩን የፅሁፍ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በመፈተሽና በማነፃፀር መቅረቡ ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ በአየር ጤና እና በክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ፅሁፍ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ንፅፅር ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በመሆኑም ጥናቱ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው የአጠናን ዘዴ መጠናዊ ምርምር(quantitatitve) እና አይነታዊ ምርምር ዘዴ (qualitative) ነው። አቀራረቡም ገላጭ ምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ አጥኚዋ ላነሳችው ጥያቄ መልስ ለማግኘት በክላሳ ድርሳን ላይ ምሁራን ለንባብ ያበቋቸውነው መጻህፍት  መሰረት በማድረግ ነው። ገለፃ ስልት የመከተሉ ምክንያት የጥናቱ አጋዥ የሆኑ  መረጃዎችን በምልከታና፣ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ በመሆናቸው ይህንን ለማድረግ የገለጻ ስንት አመቺ በመሆኑ ነው። ከዚህ በታች በናሙናነት የተመረጠው ክልል፣ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ ተጠኚ መምህራን፣ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎችና መምህራን እና መረጃዎቹ የተተነተኑበት ስልት ቀርቧል።

## 3.1 ናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ክልል አመራረጥ በተመለከተ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ፅሁፍ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችን በንፅፅር በማቅረብ አዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር አላማ ተኮር ናሙና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል። ክልሉ ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ምክንያት ፡-

1ኛ. አጥኚዋ በምትሰራበት ክልል በመሆኑ መረጃዎችንና ትብብር በቀላሉ ማግኘት በመቻሏ፤

2ኛ. በክልል ስትሰራ በቆየችባቸው ዓመታት የመምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ አተገባበር ችግሮችን በማየቷ፤

### 3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካሉት ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ የግል እና አንድ የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ለመምረጥ በመጀመሪ የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር የሚገኙት አስራ አንድ ክፍለ ከተሞች ስም እኩል መጠን ባላቸው ወረቀት ተጠቅልሎ ከተጻፉ በኃላ የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በተራ እጣ እንዲወጣ ተደርጓል፡

፡ በመቀጠል በተመሳሳይ መልኩ ከሁለቱ ክ/ከተማዎች መካከል በኮልፌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ካሉት የመንግስት ት/ቤቶች መካከል አየር ጤና 2ኛ ደረጃ ት/ት ተመርጧል፡፡ ከግል ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ት ቤት ደግሞ ክሩዝ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡ መረጣው የተከናወነበት ምክንያት በክ/ከተማው በርካታ ትምህርት ቤቶች ያሉ በመሆናቸው ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ በእጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡበት ምክንያት ዘዴው እኩል እድል ለመስጠት አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካሉት አስር ክፍለ ከተሞች የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤት መረጣ ከተከናወነ በኃላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው የክፍል ደረጃ መወሰን ነው፡፡ በመሆኑም በተወሰኑት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤቶች ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል ብቻአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥ ቢሆንም የዘጠኘኛ ክፍል የአላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ስልት (perpessive sampling method) በመጠቀም ተመርጧል፡፡ ክፍሉ የተመረጠበት ምክንያት ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች መካከል አስረኛ እና አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸው በትምህርት ቤቱ የሚቆዩበት ጊዜ እና አጭር በመሆኑና መረጃውን ለማሰባሰብ እንዳልብ ሊገኙ የማይችሉ ሲሆን ከዘጠነኛ ና ከአስራ አንደኛ ክፍል ደግሞ አስራ አንደኛ ክፍል በተመረጡት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች  በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ፣ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ግን እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ የሚገኙ በመሆኑ፣ እንዲሁም በሁሉም ትምህርት ቤቶች እንደ ልብ በሚፈልገው መጠን በመገኘቱ ተመርጠዋል፡፡

#### 3.1.4 የመምህራን አመራረጥ

ለጥናቱ ከተመረጡት የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል ከክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ አንዱ ሁለት ወንድ እና ሁለት ሴት መምህር ክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት  ወንድ እና ሴት መምህር በድምሩ በአንድ የግል ትምህርት ቤት አራት የአማርኛ መምህራን ሲገኙ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከአየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሶስት ሴት እና ሁለት ወንድ መምህራን እንዲሁም በአየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ሶስት ሴት እና አራት ወንድ መምህራን ይገኛሉ፡፡ በሁለቱ የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ያሉት የአማርኛ መምህራን በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው ሁሉም መምህራን በጥናቱ በአጠቃላይ ናሙና ዘዴ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡ ያለው (1998፣123) በሌላው በኩል በመንግስት ትምህርት ቤቶች

የሚገኑ የዘጠነኛ ክፍል የአመረኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት በቁጥር ከግል ትምህርት ቤት የበለጡ በመሆናቸው ተመጣጣን እንዲሆኑ አመቺ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ከግል ትምህርት ቤት አራት ከመንግስትም አራት በድምሩ ስምንት መምህራን በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

### 3.1.5 የተማሪዎች አመራረጥ

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በግልና በመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛው ክፍል ጊዜ የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል መምህራን የፅህፈት ማስተማር ዘዴ አተገባበር ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ከግል ትምህርት ቤት ክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ አየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በመረጃ ሰጪነት እንዲሳተፉ ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በግሉ ትምህርት ቤት በእያንዳንዱ ክፍል 40 ተማሪዎች የሚገኙ ሲሆን፣ በመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ በእያንዳንዱ ክፍል 45 ተማሪዎች በአማካይ እንደሚገኙ ከትምህርት ቤቶቹ መረጃ ክፍል ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት እያንዳንዱ ተጠኚ መምህር ከሚያስተምርበት ክፍል አስር ወንድና አስር ሴት በድምሩ 20 ተማሪዎች በተራ እጣ ናሙና በመምረጥ ከትምህርት ቤቶቹ በአጠቃላይ 80 ተማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ፣ እጣ እንዲያወጡ በማድረግ፣ በቀላል እጣ ንሞና በመምረጥ በጥናቱ መረጃ እንዲሞሉ፣ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የተነሳውን ችግር ለመመርመር መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ተግባር ላይ የዋሉት ሦስት ዘዴዎች ሲሆኑ እነሱም፡- ምልከታ (observation)፣ የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና ለመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ በዚህ ጥናት በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆን የተመረጠው በክፍል ውስጥ የመምህራን የጽሕፈት ማስተማር ዘዴን ለመከታተልና ለመገምገም የዋለ ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ ከክፍል ምልከታው በተጨማሪም በናሙናነት በተመረጡ ተማሪዎች የሚምሉየተደራጁ የፅሁፍ መጠይቅ እና ለመምህራን የሚቀርብ የፅሁፍ መተይቅ ተዘጋጅቶ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት ጥቅም ላይ በማዋል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል፡፡ በመቀጠል ለጥናቱ ስራ የዋሉት መሳሪያዎች አጠቃቀም በቅድመ ተከተል ይቀርባል፡፡

### 3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የምልከታን ጠቀሜታ በተመለከተ ያለው (2001፣16?) ሲገልፁ፤ ‹‹ አጥኚው መረጃ ለማሰባሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚቆች ጋር ወይም አካባውን በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ከቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው›› ሲሉ በተጨማሪም Robert (2003፣21) እንደገለፁት፣ ‹‹ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት የሚያገለግለው አጥኚው በተጠኚዎች ቦታ በመገኘት፣ በማየትና በመመዝገብ የሚሰበስቡ መረጃዎች ሲኖሩ ነው›› ይላሉ፡፡ የምሁራን ገለጻ የሚያስረዳው ምልከታ ጥናት የሚያደርግ ሰው መረጃዎችን መሰብሰብ የሚቻልበት መንገድ መሆኑን ያሳያል፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ እንደ ጥናቱ አይነት ተለያየ በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለዚህ ጥናት ውስን ምልከታ የምንለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረገው መማር ማስተማር ሂደት ላይ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ቀደም ብሎ በመምረጥ ወይም ጥናቱ በሚካሄድበት ርዕስ የሚያደርጉትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰጠ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበሰብበር ዘዴ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ መረጃ መሣሪያ የተመረጠበት ምክንያት የመምህራን የፅሁፍ ማስተማሪያ ዘዴ ለመመልከት በተዘጋጀ ሰነድ አማካኝነት በአጭር ጊዜ እና ከአነስተኛ ወጭ ድርጊቱን ለመከታተል አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ የምልከታ ቅፁ የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸው ሃሳቦች፣ ትላዋች መሰረት በማድረግ የተደራጀ ሲሆን፣ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ከጥናቱ ጋር ተጣጥሞ ከተዘጋጀ፣ በጥናቱ አማካሪ ከተመረጠ ናሙና ማሻሻያ ከተደረገበት በኃላ በስራ ላይ ውሏል፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው በአቀራረቡ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ የመምህራኑ የፅሁፍ ማስተማር ዘዴ ትኩረት የተሰጣቸው የመምህሩ ተግባራት በምልከታ ወቅት አለ/የለም በሚል በተዘጋጀ ማመሳከሪያ ሰነድ ላይ ባለው ሳጥን ውስጥ የ << ✓>> ምልክት በማድረግ መረጃው እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ምልከታው ተማሪዎችን ምሁራን ስነ-ጽሁፍ በማስተማር ሂደት መምህሩ ተግባራቱን ተግባራዊ ማድረጉን የምልክት ቅፁን መሰረት በማድረግ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ መምህራን መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ለሶስት ለሶስት ክፍል ጊዜያት የታየ ሲሆን ውጤትም እንዲያዝባቸው ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ምልከታውን የበለጠ አስተማማኝ እና ከአጥኚው ግላዊ ስሜት የጸዳ ለማድረግ በምልከታ ወቅት የሚያሳትፉ ሁለት ረዳት ተመልካች መምህራን ሲኖሩ ለመምህራኑ ስለ

ምልከታው ቅፅ አመዘጋገብና ውጤት አያያዥ ገለፃ  ከተደረገባቸው በኃላ ቅፁን እንዲሞሉ በማድረግ ውጤቱም ከአጥኚው ውጤት ጋር ተዳምረው እንደሚዘገቡ ከተደረገ በኃላ አማካይ ውጤቱንም እንዲሰላ ተደርጓል፡፡

ረዳት ተመልካች አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በክፍል ውስጥ የመምህራኑ ፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ተግባራትን ለመመልከት አንድ ሰው ብቻውን በቂ ባለመሆኑ የጥናቱን አስተማማኝነቱን ከፍ ለማድረግ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪ ዲግሪ ያላቸው መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

## 3.2.2 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት የማያስፈልጉ መረጃዎችን /ማሰባሰብ ያግዛል ተብሎ የተመረጠ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነው፡፡ መጠይቁ የተዘጋጀው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ምን እንደሚመስል በእነሱ እይታ እንደሚገመግሙ በማድረግ ከምልከታ የተገኘውን ውጤት አስተማማኝ ከፍ ለማድረግ ለተማሪዎች ፅሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ በአማካሪዬ ታይቶ ፣ ተገምግሞ ተስተካክሎ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡ ፡ የፅሁፍ መጠይቁ ምሁራን ካደረጓቸው ጥናቶችና ትኩረቶች በመነሳት የመምህራን ጽሕፈት ማስተማር ዘዴ በተመለከተ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የታሰቡ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ተማሪዎች የስነ የፅኑፍ መጠይቅ እንደሞሉ የተደረገበት ዋና ምክንያት ከተማሪዎች ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዜያት ስለሚያሳልፉ የመምህራቸው ስነ ጽሁፍ ማስተማሪያ ዘዴ በተመለከተ ምን እንደሚመስል የበለጠ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡ ለተማሪዎች የቀረበው የመፅሁፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች አሉት፤ የመጀመሪያው ክፍል  የተማሪዎችን አጠቃላይ መረጃ (ፆታ፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ትምህርት ቤት) ያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በመምህራን የፅሁፍ ማስተማር ወቅት መምህራኑን  ማስተማሪያ ዘዴ የተመለከቱት ጥያቄዎች ሲሆኑ በክፍል ሶስት የቀረበው በመምህራን ፅሁፍ  ማሳተማሪያ ዘዴን በተመለከተ አስተያየት የሚሰጡበት ክፍት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ለተማሪዎች የቀረበው ፅሁፍ መጠይቅ ለምልከታ ከቀረበው ሰነድ ጋር ተመሳሳይነት ለው ሲሆን በአጥኚው አማካሪ ከተገመገመ በኃላ በአማካሪው አስተያየጥ ተሻሽለው በስራ ላይ ውለዋል፡፡ በግምገማ ወቅት የተሳተፉት ተማሪዎች ብዛት ሰማንያ ወንድ እና ሰማንያ ሴት በድምሩ 160 ተማሪዎች ሲሆን፣ ተማሪዎች እጣ እንዲያወጡ በማድረግ፣ ቀላል እጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ በመጨረሻ አጥኚው ለተማሪዎች ስለመጠየቁ አስፈላጊውን ገላጻ በመስጠት መጠይቁን እንዲሞሉ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሰረት መተይቆቹ ላይ መጠነኛ ግድፈገት

ቢኖርም ጥናቱ ላይ ችግር የማያስከትል ስለመሆኑ ተስተካክሎ ሙሉ ለሙሉ በስራ ላይ ውሏል፡፡

### 3.2.3 የመምህሩን ፅሁፍ መጠይቅ

ለመምህራኑ የተዘጋጀው ፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገው መረጃዎችን ለማሰባሰብ ያግዛል ተብሎ የተመረጠ ሌላው አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነው፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ ዋና ዓላማው የጥናቱን ውጤት ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማሰባሰብና የጥናቱን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ነው፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ የተዘጋጀው ለስምንት መምህራን ሲሆን ለመምህሩ የተዘጋጀው የፅሁፍ መተይቅ ሶስት ክፍሎች የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው መምህሩን ዳራዊ መረጃ (ፆታን፣ ዕድሜ፣ ትምህርት ቤት የትምህርት ደረጃ ወዘተ) የያዘ ነው፡፡ ክፍል ሁለት በመምህራኑ ፅህፈት ማስተማር ወቅት የመምህራኑን ተግባራት የሚያመለክት ባለአምስት አማራጭ እና ‹‹ አዎ›› አይደለም፡፡ የሚል አማራጭ መልሶች የቀረቡበት ክፍል ሲሆን በመጨረሻ በክፍል ሦስት የቀረበው በመምህራኑ ማስተማር ወቅት አተገባበራቸውን የሚፈትሽ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

መጠይቁ መምህራኑ ፅህፈት በሚያስተምሩበት ወቅት በተመለከተ በተዛማች ፅሁፎች ምሁራን የጠቀሷቸውን ሃሳቦች መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የጥያቄዎቹን አስተማማኝነት የበለጠ ለማረጋገጥ በአጥኚው አማካሪ ከተገመገመ በኃላ ተሻሽሎ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የፅሁፍ መጠይቁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ በተጠኚነት ለተመረጡት መምህራን ተሰራጭተው በትክክል ተሞልተው እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ክፍል በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት በክፍል ውስጥ ምልከታ እና የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን የሚተነተኑበት ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተነሱ አበይት ጥያቄዎችን ለመመለስና የተሰበሰበውን መረጃ ለመተርጎም በተመረጡ መተንተኛ መሣሪያዎች አማካኝነት ልዩ ልዩ ስታስቲካዊ ስልቶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በዘህ መሰረት ከመምህራኑ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመቶኛ/በፐርሰንት/ እየተሰሉ ይተነተናሉ፡፡ በተጨማሪም ከመምህራን የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከተማሪዎች ፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት በባለሙያ በመታገዝ በ SPSS ስታትስቲካዊ ስሌት መረጃው ከተሰበሰበ በኂ ይዳረጋል፡፡ እንዲሁም

በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ያገኙት አማካኝ ውጤት ይነፃፀራሉ፡፡ ከግል እና ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሻለ የጽሕፈት ማስተማር ዘዴ ያላቸውን መምህራንየመለየት ስራ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም የልዩነት ደረጃውን ለማወቅ የቲ-ቴስት ውጤት ተሰልቶ ከሠንጠረዥ ዋጋው ጋር በማነጻጸር ከግል እና ከመንግስት ት/ቤቶች ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሕፈት ማስተማር ችሎታ የትኞቹ የተሻሉ መሆኑን የመለየት ተግባር ይከናወናል፡፡ በዚህም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል የመምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ መካከል ያለውን የልዩነት ደረጃ ጎልህ መሆን አለመሆኑን አስተማማኝ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ለምናልባት ስህተት 5% (P-0.05) በመተው ያለውን ልዩነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በምዕራፍ ሦስት በተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ነው፡፡በመሆኑም ከምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ምልከታ የጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ እንደመሆኑ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከረዳት ተመልካች ጋር በመሆን ተከናውኗል፡፡ ነጥብ አሰጣጡን በተመለከተ በምልከታ መከታተያው ቅጽ ላይ የቀተቡት ጥያቄዎች ከተተገበሩት አዎ፤ ካልተተገበሩ የለም በሚለው ሥር የ ‹‹✓›› ምልክት በማድረግ ሲሆን ለተማሪዎች የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ደግሞ የእያንዳንዱን ይዘት ሊያሳይ በሚችል መንገድ በጣም እስማማለሁ፤ እስመማማለሁ፤ መወሰን እቸገራለሁ፤ አልስማማም እና ፈጽሞ አልስማማም በሚሉ የደረጃ መለኪያዎች ስር የ ‹‹✓››ምልክት በማድረግ ሲሆን የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ደግሞ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የመምህራንን ዳራዊ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን፤ ክፍል ሁለት ደግሞ ባለ አምስት ደረጃ መለኪያ ይዘት ሊያሳይ በሚችል መንገድ በጣም እስማማለሁ፤እስማማለሁ፤ መወሰን እችላለሁ፤አልስማማም እና ፈጽሞ አልስማማም በሚሉ ደረጃዎች መለኪያዎች በሚሉ ጥያቄዎች ሲይዝ ክፍል ሶስት ደግሞ አዎ/የለም በሚል አማራጭ ጥያቄዎች እንዲመዘን ተደርጓል፡፡ በዚህም በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈት ለማስተማር የሚጠቀሟቸው የማስተማር ዘዴዎች በምልከታ እና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከተሰላ በኋላ የክንውኑ ይዘት በድግምሽ ተከፍሎ የተገኘ አማካኝ ውጤት ስራ ላይ ውሏል በዚህም መሰረት በሂሳብ ባለሙያ በመታገዝ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍለ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈት ማስተማር ዘዴ ላይ ያላቸው ሚና በተመለከተ ልዩነት መኖር እና አለመኖሩን፤ የትኞቹ የተሻለ አተገባበር እንዳላቸውም ለማወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ወደ መረጃ ትንተና ከመሄዳችን በፊት የተጠኚ መምህራንና የተማሪዎች ዳራ በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

## 4.1 የተጠኚ መምራን እና ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ

ሠንጠረዥ 1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መረጃ

| ተ.ቁ | የት/ቤቱ አይነት | የት/ቤቱ ስም | ጾታ | ብዛት | እድሜ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑባቸው አብይ ት/ት መስክ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የግል ት/ቤት | ክሩዝ 2ኛ ደረጃ | ወ | 1 | 39 | BA | አማርኛ | 15 |
| | | | ወ | 1 | 29 | BA | አማርኛ | 8 |
| | | | ሴ | 1 | 33 | BA | አማርኛ | 12 |
| | | | ሴ | 1 | 40 | BA | አማርኛ | 20 |
| | | | ድ | 4 | - | - | - | - |
| 2 | የመንግስት ት/ቤት | አየር ጤና 2ኛ ደረጃ | ወ | 1 | 40 | BA | አማርኛ | 18 |
| | | | ወ | 1 | 30 | BA | አማርኛ | 9 |
| | | | ሴ | 1 | 38 | BA | አማርኛ | 15 |
| | | | ሴ | 1 | 35 | BA | አማርኛ | 23 |
| | | | ድ | 4 | - | - | - | - |

ካቀረበው ሰንጠረዥ የምንረዳው በግልና በመንግስት ት/ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዳራዊ መረጃ ነው፡፡ በዚህም ከጾታዊ ሥብጥር አንጻር በግልም ሆነ በመንግስት ትምህረት ቤት አራት ወንድ አራት ሴት መምህራን ሲኖሩ እድሜ በተመለከተ በግል ት/ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ከ20-40 ዓመት በመንግስት ት/ቤቶች ደግሞ በተመሳሳይ ከ30-40 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ አገልግሎት ዘመንን በተመለከተ በግል ት/ቤት ከ8-20 ሲሆን ፤ በመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ ከ9-23 ሲሆን ሁሉም የሰለጠኑበት አብይ የትምህርት መስክ አማርኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ የቀረበው መረጃ የሚያሳየን በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ ጋር በጾታ በእድሜ ፤ትምህርት ደረጃ የአገልግሎት ዘመን የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ያለውን ልዩነት ሲነጻጸር የጎላ ልዩነት

የሌለው መሆኑና መምህራኑ በክፍል ውስጥ ጽሁፍ ለማስተማር ያላቸው ዳራ ተቀራራቢነት ያለው በመሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያመጣ መገምገም ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ 2 የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎች ዳራዊ መረጃ

| ተ.ቁ | የት/ቤቱ አይነት | የት/ቤቱ ሥም | ምድብ | ጾታ | | | እድሜ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወ | ሴ | ድ | 13-15 | 16-18 | 19 በላይ | 20 |
| 1 | የግል ት/ቤት | ክሩዝ ት/ቤት | A | 10 | 10 | 20 | 14 | 6 | - | 20 |
| | | | B | 10 | 10 | 20 | 15 | 5 | - | 20 |
| 2 | የመንግስት ት/ቤት | አየር ጤና ት/ቤት | A | 10 | 10 | 20 | 12 | 8 | - | 20 |
| | | | B | 10 | 10 | 20 | 14 | 5 | - | 20 |
| | | | | | | | | | ድምር | 80 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የጽፍ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎችን ዳራዊ መረጃ ሲሆን ይኸውም 40 ወንድ 40 ሴት በድምሩ 80 ተማሪዎች ሲሆኑ እድሜያቸውን ስንመለከት በመካከላቸው የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡ በአጠቃላይ ከሰንጠረዡ የምንረዳው የተማሪው ፆታ እና እድሜ ተቀራራቢነት ያለው በመሆኑ ውጤት ላይ ተጽዕኖ የማያመጣ መሆኑ ነው፡፡

## 4.2 ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ሠንጠረዥ 3 የመምህራን የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴ አጠቃቀም

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | የመንግስት መምህራን | | የግል መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ሳስተምር የተለያዩ የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴዎችን እጠቀማለሁ | በጣም እስማማለሁ | - | - | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 2 | 50%2 | 2 | 50% |
| | | መወሰን አልችልም | 1 | 25% | - | - |
| | | አልስማማም | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | በፍፁም አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ የፅሁፍ መጠይቁን ከሞሉት አራት መምህራን መካከል ሁለቱ 50% የሚሆኑት የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴን በመጠቀም እንደማያስተምሩ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ አንዱ 25% መወሰን መቸገሩን፤ የቀረው አንዱ 25% ደግሞ የፅህፈት ማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ እንደማያስተምር ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩና መጠይቁን በመሙላት ምላሽ ከሰጡት አራት መምህራን መካከል ሦስቱ 75% የሚሆኑት ብዙ ጊዜ የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴን በመጠቀም ፅህፈት እንደሚያስተምሩ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪው አንዱ 25% ደግሞ የፅህፈት ማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ እንደሚያስተምር ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የመረጃውን ውጤት ስናነፃፅር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴን ተጠቅመው ብዙ ጊዜ በመተግበር በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን የቀረበው መረጃ ውጤት ያሳያል፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅትም በአጥኚውና በረዳት ገምጋሚው የተገኘው ውጤት እንዲሁም የተማሪዎች ግምገማ ውጤት የተገኘ መረጃ ውጤትም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሰንጠረዥ 4 ስለ ጽሑፍ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ እውቀት መኖር

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | የመንግስት መምህራን | | የግል መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 2 | ጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ ላይ በቂ እዉቀት አለኝ | በጣም እስማማለሁ | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 1 | 25% | 2 | 50% |
| | | መወሰን አልችልም | 1 | 25% | - | - |
| | | አልስማማም | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | ፈጽሞ አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

ከፍ ሲል ከቀረበዉ ሰንጠረዥ እንደምንመለከተዉ የጽሑፍ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ እዉቀት መኖርን በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት እና በመንግስት ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ መምህራን ለቀረበዉ የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ነዉ። በመሆኑም በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሁለቱ 50% የሚሆኑት ስለ ጽሑፍ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ እዉቀት እንዳላቸዉ ምላሽ ሲሰጡ አንዱ 25% መወሰን መቸገሩን ቀሪዉ አንዱ 25% መምህር ደግሞ በቂ ስልጠና አለመዉሰዱን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል መጠይቁን ከሞሉት የግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩመምህራን መካከል ሶስቱ 75% የሆኑት ስለ ጽሑፍ ማስተማሪያ ዘዴ በቂ እዉቀት እንዳላቸዉ ምላሽ ሲሰጡ፣ አንዱ 25% ደግሞ በቂ ስልጠና አለመዉሰዱን ምላሽ ሰቷል። በአጠቃላይ ከቀረበዉ መረጃ ዉጤት የምንረዳዉ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ሲነጻጸሩ በተሻለ ሁኔታ ስለ ጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ በተሻለ ሁኔታ በቂ እዉቀት ያላቸዉ መሆኑን ከቀረበዉ መረጃ መረዳት ይቻላል።

## ሰንጠረዥ 5 የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን እንዲጽፉ ማድረግ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | የመንግስት መምህራን | | የግል መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 3 | የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን እንዲጽፉ አደርጋለሁ | በጣም እስማማለሁ | - | - | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 3 | 75% | 1 | 25% |
| | | መወሰን አልችልም | 1 | 25% | - | - |
| | | አልስማማም | - | - | 2 | 50% |
| | | ፈጽሞ አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

ከቀረበዉ ሰንጠረዥ እንደመምንመለከተዉ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን ተማሪዎች እንዲጽፉ ስለማድረግ ለቀረበላቸዉ የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ ለጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ከሰጡት አራት መምህራን መካከል ሶስቱ 75% የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን እንዲጽፉ እንደሚያደርጉ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዉ አንዱ 25% መምህር ደግሞ መወሰን መቸገሩን ምላሽ ሰቷል፡፡ በሌላ በኩል በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሁለቱ 50% የሚሆኑት መምህራን ለተማሪዎች የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን እንዲጽፉ እንደሚያደርጉ ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት መረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የቀረበዉ የመረጃ ዉጤት የሚያስረዳዉ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን እንዲጽፉ ከማድረግ አንጻር በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸዉ ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት መረዳት የቻላል፡፡

ሰንጠረዥ 6 በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን እሰጣለሁ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | የመንግስት መምህራን | | የግል መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 4 | በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን እሰጣለሁ | በጣም እስማማለሁ | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 3 | 75% | 2 | 50% |
| | | መወሰን አልችልም | - | - | - | - |
| | | አልስማማም | - | - | 1 | 25% |
| | | ፈጽሞ አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

ከቀረበዉ ሰንጠረዥ እንደመምንመለከተዉ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ አራት መምህራን ለተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን ስለመስጠት ለቀረበላቸዉ የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ ለጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ከሰጡት አራት መምህራን መካከል አራቱም 100% የሚሆኑት ለተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን ስለመስጠት ምላሽ ሲሰጡ፣ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል አራቱ ደግሞ ሶስቱ 75% የሚሆኑት መምህራን ለተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን እንደሚሰጡ ምላሽ ሲሰጡ፤ ቀሪዉ አንዱ 25% ግን እንደማይሰጡ ምላሽ ስጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ የቀረበዉ የመረጃ ዉጤት የሚያሳየን በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን የመስጠት የተሻለ አተገባበር እንዳላቸዉ ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ 7 ለተማሪዎች በወቅቱ ምጋቢ ምላሽ ስለመስጠት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | የመንግስት መምህራን | | የግል መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 5 | ለተማሪዎች በወቅቱ ምጋቢ ምላሽ እሰጣለሁ። | በጣም እስማማለሁ | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 1 | 25% | 2 | 50% |
| | | መወሰን አልችልም | 1 | 25% | - | - |
| | | አልስማማም | 1 | 25% | 1 | 25% |
| | | ፈጽሞ አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

እላይ ከቀረበዉ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለዉ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን ለተማሪዎች ለሚሰጡት የጽሕፈት ስራ በወቅቱ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ለቀረበላቸዉ የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ነዉ።በመሆኑም በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሁለቱ 50% የሚሆኑት ለተማሪዎች በወቅቱ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ምላሽ ሲሰጡ አንዱ 25% መወሰን መቸገሩን ሌላዉ ቀሪዉ አንዱ 25% መምህር ደግሞ በወቅቱ ምጋቤ ምላሽ መስጠት እንደማጥሰጥ ምላሽ ሰቷል።

በሌላዉ በኩል መጠይቁን ከሞሉት በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ አራት መምህራን መካከል ሶስቱ 75% የሚሆኑት ለተማሪዎች በወቅቱ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዉ አንዱ 25% መምህር ደግሞ በወቅቱ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጥ ምላሽ ሰቷል በአጠቃላይ ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት የምንረዳዉ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ሲነጻጸሩ ለተማሪዎች ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት የተሻለ መሆናቸዉን ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት መረዳት ይቻላል።

**ሰንጠረዥ 8 የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል መመዘን፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቂ | አማራጮች | የመንግስት መምሕራን | | የግል መምሕራን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 6 | የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል እመዝናለሁ፡፡ | በጣም እስማማለሁ | - | - | 1 | 25% |
| | | እስማማለሁ | 3 | 75% | 3 | 75% |
| | | መወሰን አልችልም | - | - | - | - |
| | | አልስማማም | 1 | 25% | - | - |
| | | ፈጽሞ አልስማማም | - | - | - | - |
| | | ድምር | 4 | 100% | 4 | 100% |

ከቀረበዉ ሰንጠረዥ የምንረዳዉ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት አራት መምህራን መካከል ሶስቱ 75% የሚሆኑት የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል እንደሚመዝኑ፣ ቀሪዉ አንዱ 25% መምህር ደግሞ እንደማይመዝን መረጃዉ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩና መጠይቁን በመሙላት ምላሽ ከመስጠት አራቱ መምህራን መካከል አራቱም 100% የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግልና በቡድን እንደሚመዝኑ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ የቀረበዉን የመረጃ ዉጤት ስናነጻጽር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን በተሸለ የተማሪዎችን ችሎታ ለማዎቅ በግልና እንደሚመዝኑ ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.3 ከክፍል ምልከታና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

በዚህ ክፍል ከምልከታና ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት በስድስት ዋና ዋና ነጥቦች የተከፈሉ ሃያ ሰባት ጥያቂዎችን መሠረት በማድረግ ግምገማ ተካሂዳል፡፡ በመጨረሻም ከሁለቱምየመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኘው መረጃ ውጤት ነጥብ በአማካይ የቲ-ስሌት ዋጋ በማስላት የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የተገኘውን ውጤት በቅደም ተከተል በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

### 4.3.1. የመምህሩ የፅህፈት ትምህርት እቅድ

በፅህፈት ትምህርት ሂደት መምህራን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ማስተማር የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ፅህፈትን ለማስተማር ሲያቅዱ ማከናወን ከሚገባቸው ተግባራት መካከል አምስት ነጥቦች በምዕራፍ ሁለት በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝትተጠቅሷል እነዚህም ነጥቦች የመምህሩ እቅድ አጋጅቶ ክፍል መግባት፣ የትምህርቱን ዓላማ በሚገባ ማስተዋወቅ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመገምገም እቅድ ማዘጋጀት፣ የክፍሉን ሁኔታ ለመቆጣጠር ማቀድን እና በክፍል እና ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ስራዎችን ለመስጠት አቅደዋል የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ነጥቦች መሠረት በማድረግ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ መምህራንላይ በተደረገ ምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በቀጣይ ሠንጠረዥ ይቀርባል፡፡

ሠንጠረዥ 9 የመምህራን ትምህርት እቅድ አያያዝ አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት

| የተጠኚ መመህራን ትምህርት ቤት | የክፍል ምልከታ ውጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 4.157 | 3.072 | አለው | 4.022 | 4.369 | አለው |
| የመንግስት | 3.460 | | | 3.827 | | |
| | ቲ-ጣሪያ 2.447 | | | ቲ - ጣርያ 1.976 | | |

እላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ትምህርት እቅድ በተመለከተ የተደረገውን የክፍልውስጥ ምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ላይ በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው አማካይ ውጤት 3.460 ሲሆን በግል ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ 4.157 ነው፡፡ የተገኘው ውጤት ሲነፃፀር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ያገኙት አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ በእቅድ አዘገጃጀት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ልዩነት የጎላ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ በቲ-ስሌት ቀመር ተፈትሾ3.072 ውጤት ተገኝቷል፡፡ ይህ ውጤት ከቲ-ጣርያው 2-447 ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ሆኖ በመገኘቱ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ደግሞ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ውጤት 3.827 ሲሆን በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ 4.022 ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ውጤት መሰረት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ይልቅ የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ ማቀድ ተግባር የተሻሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተገኘው ውጤት በቲ-ቴስት ተፈትሾ 4.369 ውጤት የተገኘ ሲሆን፣ ከቲ-ጣርያው ውጤት 1.976 በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከተገኘው የውጤት መረጃ በመነሳት የቲ-ስሌት ዋጋ ከቲ-ጣርያው ከበለጠ በመምህራኑ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን እንረዳለን በተቃራኒው የቲ-ጣሪያ ውጤት ከቲ-ስሌት በልጦ ከተገኘ ወይም የቲ-ስሌት ከቲ-ጣርያ አንሶ ከተገኘ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን እንረዳለን፡፡ በዚህ ቀመር መሰረትም የቲ-ስሌት ዋጋው ከቲ-ጣሪያው በልጦ በመገኘቱ በመምህራኑ የፅህፈት ትምህርት እቅድ አዘገጃጀት የታየው ልዩነት አስተማማኝ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በፅህፈት ማስተማር ሂደት ማቀድን በተመለከተ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን መረጃ ለማግኘት በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ በአጥኚዋ እና ረዳት ተመልካች ገምጋሚው ማረጋገጥ እንደተቻለው በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ፅህፈት ለማስተማር እቅድ እንደሚያዘጋጁ ነገር ግን፤ ከላይ ለተገለፀው የውጤት ልዩነት መኖር መንስኤ የሆኑት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የክፍሉን ሁኔታ ለመቆጣጠር ማቀድ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመገምገም ማቀድ የሚሉት ነጥቦች በእቅዳቸው ያለመካተት ችግሮች በመታየታቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝ 2.52 እነዚህ ተባባላት መኪናውን እንዳለባቸው ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ለልዩነት መፈጠር ምክንያቶች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ለተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ውጤት በልጦ በመገኘቱ ፅህፈት በማስተማር ዘዴ የመምህራን እቅድ ዝግጅት በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩት መምህራን በመጠኑ የተሻለ አተገባበር እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.3.2 የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ስለመስጠት

መምህራን ፅህፈትን ለማስተማር የሚጠቀሟቸው ዘዴዎች በተመለከተ የተማሪዎችን የፅህፈት ችሎት ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ምን መምሰል እንዳለባቸውና እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

በዚህ ክፍል በቀጣይ በሚቀርቡት ነጥቦች አማካኝነት የመምህራኑ ለተማሪዎች የፅህፈት ችሎታቸውን የሚያሻሽሉበት መልመጃዎችን መስጠት አለመስጠት ተፈትሿል የቀረቡት ነጥቦች፡- የራስን ገጠመኝና ልምድ፣ የዕለት ክንውኖች ወዘተ ተነስተው የሚሰሩ ስራዎችን መምህሩ ሰጥተዋል፣ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን ግጥም፣ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ እና ግጥምን ወደ ዝርው ዝርውን ወደ ግጥም ቀይረው እንዲፃፉ ያደርጋሉ፣ አንድን ፅሁፍ አሳጥረው ወይም አስረዝመው እንዲፃፉ ያደርጋሉ የሚሉ ነጥቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ነጥቦች መሠረት በማድረግም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ላይ በተደረገው የክፍል ምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው የመረጃ ውጤት በቀጣይ ሠንጠረዥ ይቀርባል፡፡

**ሠንጠረዥ 10 ለተማሪዎች የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን መስጠት አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት**

| የተጠኚ መመህራን ትምህርት ቤት | የክፍል ምልከታ ውጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 4.35 | 3.777 | አለው | 4.34 | 4.498 | አለው |
| የመንግስት | 3.997 | | | 3.870 | | |
| | ቲ-ጣሪያ 2.447 | | | ቲ - ጣርያ 1.976 | | |

ከዚህ ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው በመንግስት እና በግል ትምህርትቤቶች በተደረገው የክፍል ምልከታ እና የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን 3.997፣ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ 4.35 አማካይ ውጤት እንዳስመዘገቡ ከቀረበው መረጃ መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑመ በመንግስት ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች የፅህፈት ችሎታን የሚያግዙ መልመጃዎችን በመስጠት ረገድ የተሻለ ችሎታ እንዳላቸው የተገኘው አማካይ ውጤት ያስረዳል፡

፡ በመምህራኑ ፅህፈት ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን በመስጠት ረገድ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገው ቲ-ስሌት የተገኘው ውጤት 3.777 ሲሆን፣ የቲማሪያው ዋጋ ደግሞ 2.447 በመሆኑ የቲ-ጣሪያው ከቲ-ቴስቱ አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ለተማሪዎች የቀረበውን የፅሁፍ መጠይቅ ስንመለከት ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት 3.870 ሲሆን፤ የግል ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ 4.34 አስመዝግበዋል ከተገኘው አማካይ ውጤት የምንረዳው በግል ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ ለተማሪዎች የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ከመስጠት አንፃር በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል ለማለት ይቻላል፡፡ በተገኘው ውጤት አማካኝነት የተፈጠረውን የልዩነት ደረጃ ምን ያህል መሆኑን ለማወቅ በተደረገው የቲ-ስሌት የተመዘገበው ውጤት 4.498 ሲሆን የቲ-ጣርያው ዋጋ ደግሞ1.976 ነው ውጤቱን በምናነፃፅርበት ጊዜ የቲ-ስሌቱ ዋጋ ከቲ-ጣርያው ዋጋ በልጦ በመገኘቱ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት እንዳለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተገኘው ውጤት በተጨማሪም ለልዩነቶቹ መፍጠር የሚጠቀሱት ምክንያቶች በክፍል ምልከታ ወቅት በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንና ተማሪዎች የራስን ገጠመኝና ልምድ እና የእለት ክንውኖችን በተመለከተ የሚሰሩ ስራዎችን፣ ግጥምና ድርሰት መፃፍ፣ ግጥም ወደ ዝርው ዝርውን ወደ ግጥም መፃፍ፣ ፅሁፍን አሳጥሮና አስይዞም በሚፃፍ አተገባበር አንፃር የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው አጥኚዋና ረዳት ተመልካቿ አማካኝነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.3.3 የመምህሯ ፅህፈትን ለማስተማር ግልፅ መመሪያ ስለመስጠት

በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት እንደተገለፀው መምህራን በፅህፈት ትምህርት ወቅት ተማሪዎች የፅህፈትን ሥራ በተገቢው መንገድ መስራት እንዲችሉ ግልፅ መመሪያ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል በቀጣይ በቀረቡት ነጥቦች አማካኝነት የመምህሩ ፅህፈትን ሲያስተምሩ ግልፅ መመሪያ መስተት አለመስጠታቸው ይፈተሻል፡፡ የቀረቡት ነጥቦች፣ ስለፅለቱ ትምህርት ግልፅ መመሪያ መስጠት፣ ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሲሰሩ ግል መመሪያ ማቅረብ፣ የተሰጣቸው መልመጃ በግልፅ ሀሳባቸውን የሚያስችላቸው ስለመሆኑ፣ አንዱ ተማሪ የሌለውን እያየ እንዲተራረሙ ማድረግ አስተዋፅዖ አዘጋጅተው ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ፣ ተማሪዎች ሲሰሩ እየዞሩ ይከታተላሉ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ነጥቦች መሰረት

በማድረግ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ላይ በተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በቀጣይ ሰንጠረዥ ይቀርባል፡፡

ሠንጠረዥ 11 መምህሩ/ሯ ግልፅ መመሪያ መስጠት አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት

| የተጠኚ መመህራን ትምህርት ቤት | የክፍል ምልከታ ውጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 3.712 | 2.051 | አለው | 3.87 | 3.424 | አለው |
| የመንግስት | 2.879 | | | 3.509 | | |
| | ቲ-ጣሪያ 2.447 | | | ቲ - ጣርያ 1.976 | | |

ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው በመንግስትና በግል ት/ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በፅህፈት ትምህርት ወቅት ግልፅ መመሪያ መስጠት ያስመዘገቡትን ውጤት ነው፡፡ የመንግስት ትምህርትቤቶች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 2.879 ሲሆን፤ የግል ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ 3.712 መሆኑን የመረጃው ውጤት ያሳያል፡፡ ከተገኘው አማካኝ ውጤት መረዳት የሚቻለው የግል ትምህርት ቤት መምህራን በተሻለ መምህሩ ግልፅ መመሪያ የሚሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ልዩነቱ የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በቲ-ስሌት ተፈትሿል፡፡ በዚህ መሰረት የቲ-ስሌቱ 2.051 ሲሆን፤ የቲ-ጣሪያ ዋጋ 2.447 በመሆኑ እና የቲ-ስሌት ዋጋ ከቲ-ጣርያ ዋጋ አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው አማካይ ውጤት ደግሞ የመንግስት ትምህርትቤቶች አማካይ ውጤት 3.5069 ሲሆን የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ 3.87 አማካይ ውጤት አግኝተዋል፡፡ በውጤቱም የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ ለተማሪዎች ስለሚሰሩት ግልፅ መመሪያ ከመስጠት አንፃር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተሻሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጠኚዎች መካከልጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ በቲ-ስሌት ተፈትሾ የቲ-ስሌት ዋጋ 3.424 ሲሆን፤ የቲ-ጣሪያ ዋጋ ደግሞ 1.975 ውጤት ተገኝቷል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረት የቲ-ስሌት ዋጋው ከቲ-ጣሪያ ዋጋ በልጦ በመገኘቱ በመካከላቸው ያለው ልዩነት ያለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለልዩነቶቹ መፈጠር የሚጠቀሱት ምክንያቶች የግል ትምህርት ቤት መምህሩን መመሪያዎችን ለተማሪዎች ሲሰጡ በቡድንና በጥንድ ብቻ ሳይሆን በግልም ሊሰሩም እየተዟዟሩ

የሚሰጡ መሆኑ በሌላ በኩል በግል የሚያስተምሩ መምህራን ከክፍል ውጪ የሚሰሩ መልመጃዎችንም ሲሰጡ ታይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 2.2 ተማሪዎች ለሚሰጧቸው መልመጃ ግልፅ መመሪያ መስጠት እንደሚገባ ተገልፃል፡፡

### 4.3.4 የመምህሩ/ሯ የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዥ

በፅህፈት ትምህርት ሂደት የመምህሯን የተማሪዎችን የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ በተመለከተ ምን መምሰል እንዳለበት በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 2.5 ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ክፍል በቀጣይ በሚቀርቡት ነጥቦች አማካኝነት የመምህራኑ የፅሀፈት ውጤት አያያዞ ተፈትሿል፡፡ ነጥቦቹም ተማሪዎችን መገምገሚያ መስፈርት አዘጋጅተው ተማሪዎችን ይመዝናሉ፤ የምዘና መስፈርቶችን ያሳውቃሉ፤ የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በማየት በግል ይመዝነሉ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ነጥቦች መሰረት በማድረግ በክፍል ምልከታ እና በተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በቀጣይ ሰንጠረዥ ይቀርባል፡፡

## ሠንጠረዥ 12 የመምህሩ/ሯ የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ አማካይና ቲ-ስሌት ውጤት

| የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤት | የክፍል ምልከታ ውጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 3.360 | 3.901 | አለው | 3.697 | 2.753 | አለው |
| የመንግስት | 3.044 | | | 3.427 | | |
| | ቲ-ጣሪያ 2.55 | | | ቲ - ጣርያ 1.95 | | |

ከቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህሯን የተማሪዎች ፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ ነው፡፡ የግል ትምህርት ቤት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 3.360 ሲሆን፤ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ3.044 መሆኑን የመረጃው ውጤት ያሳያል፡፡ ከተገኘው የመረጃ ውጤት መረዳት የሚቻለው የግል ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ ውጤት አያያዝ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ልዩነቱ የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማወቅበቲ-ስሌት ተፍሿል፡፡ በዚህ መሰረት የቲ-ስሌቱ 3.901 ሲሆን፤ የቲ-ጣርያው 2.455 በመሆኑና የቲ-ስሌት ዋጋው ከቲ-ዋጋው በልጦ በመገኘቱ በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤት አማካይ ውጤት 3.927 ሲሆን፤ የግሉ ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት ደግሞ 3.697 አማካይ ውጤት አኝተዋል፡፡ በውጤቱም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ በፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተሻሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ልዩነቱ የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በቲ-ስሌት ተፈትሿል፡፡ የቲ-ስሌት ዋጋ 2.753 ሲሆን የቲ-ጣሪያ ዋጋ ደግሞ 1.95ውጤት ተገኝቷል በተገኘው ውጤት መሰረት የቲ-ስሌት ዋጋው ከቲ-ጣሪያው በልጦ በመገኘቱ በመካከላቸው ያለው ልዩነት ጉልህ ልዩነት ደረጃ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ለልዩነቶች መፈጠር የሚጠቀቡት ምክንያቶች በአጥኚውና በረዳት ተምካች ማረጋገጥ እንደተቻለው የግል ትምህርት ቤት መምህራን የፅህፈት መመዘኛው ቤት በሚይዙበት ጊዜ የምዘና መስፈርቶችን ለተማሪዎች ከማሳወቅ በተጨማሪ በግልና በቡድን ተማሪዎችን ሲመዝኑ ታይተዋል፡፡ በሌላ በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ተጠሪን በግል በመመዘን በቡድን ምዘና ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ በተዛማጅፅሁፍ ቅኝት 2.5 ተማሪዎችን በግልም በቡድንም መመዘን ተገቢ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

### 4.3.5 የመምህራን ግብረ መልስ አሰጣጥ

ፅህፈት በማስተማር ሂደት መምህራን ግብረ መልስ መስጠት ከሚገባቸው ተግባራት ውስጥ ሦስት ነጥቦች ተካተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህም በወቅቱ ለተማሪዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣ ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠትና በትምህርቱ መጨረሻ ማጠቃለያ መስጠት የሚሉት ናቸው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 2.43 ቀርቧል፡፡ እነዚህን ነጥቦች መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ውጤት በቀጣይ ሠንጠረዥ ይቀርባል፡፡

**ሠንጠረዥ 13 ግብረ መልስ አሰጣጥ አማካኝና ቲ-ስሌት ውጤት**

| የተጠኚ መመህራን ትምህርት ቤት | የክፍል ምልከታ ውጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ-ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 4.712 | 4.401 | አለው | 4.462 | 4.341 | አለው |
| የመንግስት | 4.112 | | | 3.873 | | |
| | ቲ-ጣሪያ 2.447 | | | ቲ - ጣርያ 1.976 | | |

ከቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ግብረመልስ መስጠት ከምልከታ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ነው። በዚህ መሰረት በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የክፍል ውስጥ ምልከታ አማካይ ውጤት 4.112 ሲሆን፤ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት ደግሞ 4.712 ነው። የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን አማካይ ውጤት በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩት መምህራን አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ በመንግስት ትምህርት ቤት አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ ግብረመልስ አሰጣጥ እንዳላቸው ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል። በጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ ውጤቱ 2.497 ሲሆን፣ የቲ-ቴስቱ ዋጋ ከቲ-ጣሪያ ዋጋ በልጦ በመገኘቱ በመምህራኑ ግብረ መልስ መስጠት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል። በዚህ መሰረት የግል ትምህርት ቤት መምህራን በመጠኑም ቢሆን ከመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ ግበረ መልስ የመሸጡት አተገባበር እንዳላቸው ከቀረበው የሠንጠረዥ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡ ፡

ከተማሪዎች የፅሁፍና መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ደግሞ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህሩን አማካይ ውጤት 3.873 ሲሆን፤ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት ደግሞ 4.462 አግኝተዋል። ይህን ውጤት ስንመለከት ከመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ይልቅ የግል ትምህት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን አማካይ ውጤት በልጦ በመገኘቱ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ግብረ መልስ አሰጣጥ የተሻለ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ልዩነት የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በቲ-ስሌት ተፈትሾ 4.341 ወጤት ተገኝቷል። ይህ ውጤት ከቲ-ጣሪያ ውጤት 1.976 ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ሆኖ በመገኘቱ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት እንዳለማረጋገጥ ተችሏል።

በተጨማሪም የተገኘውን ውጤት በክፍል ምልከታ ወቅት በአጥኚውና ረዳት ተመልካች አማካኝነት ማረጋገጥ እንደተቻለው በፅህፈት ትምህርት ወቅት ግብረ መልስ ከመስጠት አንፃር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ለተማሪዎች በወቅቱ በአፋጣኝ ምላሽ ሲሰጡ በተጨማሪም በመጨረሻ ለተማሪዎች በተሻለ ማጠቃለያ ሲሰጡ፤ የመንግስት መምህራን ግን የመሰላቸትና ወቅታዊ ግብረመልስ ማጠቃለያ ከመስጠት ይልቅ ከክፍል ለመውጣት የመቸኮል ሁኔታ እንደነበር ተስተውሏል። እነዚህ ሁኔታዎች ለተጠቀሰው ልዩነት መፈጠር ምክንያት መሆናቸውም ተጠቅሷል።

## 4.4 በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን የፅህፈት ማስተማር ዘዴ ውጤት

### 4.4.1. የፅህፈት ትምህርት አተገባበር ውጤት

በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የፅህፈት ትምህርት ወቅት የየትኞቹ ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው ለመገምገም በቀረቡት ነጥቦች አማካኝነት የትኞቹ መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው ባለፈው ክፍል ተገልጿል፡፡ዉጤቱን ለማግኘት መነሻ የሆኑ ነጥቦች፡-

- ጽሕፈት ለማስተማር ማቀድ
- የጽሕፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን መስጠት
- ጽሕፈትን ለማስተማር ግልጽ መመሪያ መስጠት
- የጽሕፈት ቸሎታ ዉጤት አያያዝ
- ግብረ መልስ አሰጣጥ

እላይ የቀረቡትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ከክፍል ምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች የተገኘዉን አጠቃላይ ዉጤት በቀጣይ ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 14 የመምህራን የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ አማካይና የቴ- ስሌት አጠቃላይ ዉጤት

| የተኚ መምህራን ትምህርት ቤት | የክፍለ ምልከታ ዉጤት | | | የተማሪዎች ግምገማ ዉጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | ቲ - ስሌት | ልዩነት | አማካይ | ቲ - ስሌት | ልዩነት |
| የግል | 4.395 | 3.587 | አለዉ | 4.121 | 3.809 | አለዉ |
| የመንግስት | 3.797 | | | 3.809 | | |
| ቲ - ጣሪያ = 2-447 | | | | ቲ - ጣሪያ = 2 -926 | | |

በሰንጠዥ የቀረበዉን መረጃ እንደምንመለከተዉ በግል እን በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የጽሕፈት ትምህርት ወቅት ያላቸዉን ሚና በተመለከተ ያስመዘገቡትን አጠቃላይ ዉጤት ነዉ፡፡ በተደረገዉ የክፍል ዉስጥ ምልከታ የመንግስት ትምህርት ቤት 3.797፤ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ 4.395 አማካይ

ዉጤት አስመዝግበዋል። በተዋሪዎች ከተወሰደዉ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጤት ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤት 3.809 ፣ የግል ትምህርት ቤት 4.121 አማካይ ዉጤት አስመዝግበዋል። ከቀረበዉ የመረጃ ዉጤት የምንረዳዉ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን አማካይ ዉጤት የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የበለጠ መሆኑን ነዉ።

በመምህራኑ መካከል የጎላ ልዩነት መኖር እና አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገዉ የ ቲ-ስሌት የክፍል ዉስጥ ምልከታ የቲ-ስሌት ዋጋ 3.587 ሲሆን ፣ የቲ-ጣሪያ ዋጋ ደግሞ 2.497 ተመዝግቧል፣ በተማሪዎች ግምገማ የተገኘዉ የቲ-ስሌት ዋጋ 3.809 ሲሆን የቲ-ስሌት ጣሪያ ደግሞ 2.976 ነዉ። በዚህም የአማካይ ዉጤቱም ሆነ የቲ-ስሌት ዉጤቱ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተመሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ዉጤት በልጦ በመገኘቱበመምህራን ጽሕፈት ማስተማር አተገባበር የግል ትምህርት ቤት መምህራን የተሸሉ እንደሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል።

4-4-2 በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ አጠቃላይ ዉጤት ፤ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች የሕጽሕፈት ትምህርት ወቅት የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ ለመፈተሸ በምዕራፍ ሁለት በምሁራን የተረጋገጡ አምስት ነጥቦች የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እነዚህን ነጥቦች መሰረት በማድረግ የክፍል ምልከታ እና ለተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች በማዘጋጅት የተገኘዉን ዉጤት በዐማካይ እና በቲ-ስሌት ተቀምሯል ። የተገኘዉን ዉጠየት ደረጃ ለመስጠትfallock and Brown (1983,29) ባቀረባቸዉ የደረጃ መለኪያ ነጥቦች አማካኝነት ዉጤት ተሰጥቷል።

### የደረጃ መለኪያ ነጥቦች፡-

በጣም ዝቅተኛ =1 — 00 — 1.80

ዝቅተኛ = 1-81 — 2.61

መካከለኛ = 2- 62 — 3.42

ጥሩ = 3 — 43 — 4.23

በጣም ጥሩ= 4- 23 — 5.00

ነሚል ደረጃ የተከፋፈሉ ናቸዉ። እነዚሕን መስፈርቶች በመጠቀም በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር አጠቃላይ ዉጤት መሰረት በየትኛዉ ደረጃ እናዳሉ ለማረጋገጥ ከክፍል ምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘዉ አማካይ ዉጤት በሚከተለዉ ሰንጠረዥ ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አስራ አምስት የመምሕራን የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ለመፈተሽ በክፍል ዉስጥ ምልከታ እና የተማሪዎች ግምገማ አማካይ ችሎታ ደረጃ መለኪያ መስፈርት አጠቃላይ የተገኘዉ ዉጤት ደረጃ።

## ሰንጠረዥ 15 የምልከታ ተማሪዎች ግምገማ አጠቃላይ ውጤት

| ተ.ቁ. | የመምህራን ሚና መፈተኛ ነጥቾ | ከምልከታ የተገኘ ዉጤት | | | | የተማሪዎች ግምገማ ዉጤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የመንግስት ት/ቤት | ደረጃ | የግል ት/ቤት | ደረጃ | የመንግስት ት/ቤት | ደረጃ | የግል ት/ቤት | ደረጃ |
| 1. | ለማስተማር ማቀድ | 3.460 | ጥሩ | 4.157 | ጥሩ | 3.827 | ጥሩ | 4.022 | ጥሩ |
| 2. | መልመጃ አሰጣጥ | 3.997 | ጥሩ | 4.35 | በ.ጥሩ | 3.870 | ጥሩ | 4.34 | በ.ጥሩ |
| 3. | መመሪያ አሰጣጥ | 2.879 | መካከለኛ | 3.712 | ጥሩ | 3.509 | ጥሩ | 3.87 | ጥሩ |
| 4. | ዉጤት አያያዝ | 3.044 | መካከለኛ | 3.360 | ጥሩ | 3.427 | ጥሩ | 3.697 | ጥሩ |
| 5. | ግብረመልስ መስጠት | 4.112 | ጥሩ | 4.712 | በ.ጥሩ | 3.873 | ጥሩ | 4.462 | ጥሩ |
| | አጠቃላይ አማካይ ዉጤት | 3.797 | ጥሩ | 4.395 | በ.ጥሩ | 3.809 | ጥሩ | 4.75 | ጥሩ |

በሰንጠረዥ የሰፈረዉን የዉጤት መረጃ እንደምንመለከተዉ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጽሕፈት ትምህርት ወቅት የሚጠቀሜት የማስተማሪያ ዘዴ በተመለከተ በቀረቡት አምስት መመዘኛ ነጥቦች አማካይነት በክፍል ዉስጥ እንደሚያመለክተዉ በክፍል ዉስጥ ምልከታ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት

የአማርኛ መምህራን ሚና በተመለከተ ለማስተማር በማቀድ፣ መልመጃ አሰጣጥ፣ግብረመልስ አሰጣጥ፣ ጥሩ ዉጤት ሲያስመዘግቡ መመሪያ እና ዉጤት አሰጣጥ መካከለኛ ዉጤት አስመዝግበዋል፡፡ በሌላ በኩል በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ምልመጃ አሰጣጥ፣ ግብረመልስ አሰጣጥ፣ በጣም ጥሩ ዉጤት ሲያስመዘግቡ፣ በማቀድ እና መመሪያ አሰጣጥ፣ ዉጤት አያያዝ ጥሩ ዉጤት አስመዝግበዋል፡፡በአጠቃላይ ከቀረበዉ መረጃ ዉጤት መረዳት የሚቻለዉ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን አጠቃላይ አማካይ ዉጤት 3.297 በማስመዝገብ ጥሩ የችሎታ ደረጃ ላይ ሲመደቡ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ደግሞ 4.395 አጠቃላይ አማካይ ዉጠት በማምጣት በጣም ጥሩ የችሎታ ደረጃ ላይ መገኘታቸዉን በዚሕም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምሕራን መንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩት መምህራን የተሸለ አተገባበር ላይ የሚገኙ መሆናቸዉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎች ግምገማ ዉጤት እንደሚያመለክተዉ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የጽሑፍ የማስተማር ዘዴ ለመመዘን በቀረቡት አምስት ነጥቦች የተገኘዉን ዉጤት ስንመለከት ፤ ለማስተማር ማቀድ፣መልመጃ አሰጣት፣ መመሪያ አሰጣጥ፣ ዉጤት አያያዝ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ ጥሩ ዉጤት ሲያስመዘግቡ ፤ የግል መምህራን ደግሞ ለማስተማር ማቀድ፣መልመጃ አሰጣት፣ መመሪያ አሰጣጥ፣ ዉጤት አያያዝ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ በጣም ጥሩ ዉጤት አስመዝግበዋል፤ አጠቃላይ ያስመዘገቡትን ዉጤት ስንመለከት የመንግስት ትምህርት ቤት አማካይ ዉጤት 3.809 በማስመዝገብ ጥሩ ደረጃ ሲመደቡ የግል ትምህርት ቤት መምህራን ደግሞ 4.25 አማካይ ዉጤት በማምጣት በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ ተመድበዋል፡፡ አጠቃላይ ከመረጃዉ እንደምንረዳዉ በክፍል ዉስጥ ምልከታም ሆነ በተማሪዎች ግምገማ ዉጤት የግል ትምህርት ቤት መምህራን ጽሕፈት በማስተማር ዘዴ የተሸለ ሰተገባበር እንዳላቸዉ በቀረበዉ የመረጃ ትንተና ዉጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ የተገኘው ውጤትና ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመፍትሄ ሃሳቦች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በአየር ጤና እና ክሩዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ በመፈተሽ በንፅፅር ማቅረብ ነው፡፡ ይህንን አብይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ይዟቸው የቀረበው ንዑሳን አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመምህራኑ ጽሕፈት የማስተማር ዘዴ አተገባበር ይፈትሻል
- የመምህራን የሚጠቀሙባቸውን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ በንፅፅር ይመረምራል
- ተማሪዎች መምህራን የሚጠቀሙባቸውን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ ምን ያህል እንደተጠቀሙበት ይመረምራል፡፡

አጥኚዋ እነዚህ ንዑሳን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሁለት ምሁራን በጥናት ያረጋገጧቸውን ንድፈ ሀሳቦች፣ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ በናሙናነት የተመረጡት ተሳታፊዎች አመራረጥ ሂደትና ለጥናቱ የተሟላ መረጃ ያስገኛሉ የተባሉ መሳሪያዎች የክፍል ምልከታ፤ ለተማሪዎች እና ለመምህራን ቀረቡ የፅሁፍ መጠይቅ አማካንነት መረጃ አሰባሰባለች፡፡ በነዚህ የመረጃ መሠብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች እንደ ዝምድናቸው በማቀናጀት በምዕራፍ አራት ተተንትነዋል፡፡ ከትንተናው የተገኘው ውጤትም በቀጣይ ይቀርባል፡ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን ፅህፈት ለማስተማር ሲያቅዱ የሁለቱን እቅድ አዘጋጅተው ከክፍል መግባት፣ የትምህርቱን አላማ ከማስተዋወቅ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመገምገም ከማቀድ አንፃር በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች በግልፅ በማስተዋወቅ ትኩረት በመስጠት እንዲዘጋጁ ሲያደርጉ፣ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ግን ግልፅ በሆነ እና በበቂ ሁኔታ ለተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት እቅድ ሳስተዋውቁ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ እንዲሁም በዕለት ትምህርት ዝግጅታቸው ከፋፍለው ያስቀመጡትን ጊዜ በአግባቡ የመፈፀም ክፍተቶችም እንደነበሩ በክፍል ምልከታ መታየቱን በመረጃው ውጤት ተረጋግጧል፡፡

- በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ከመስጠት አንፃር በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን፣ ተማሪዎች የራሳቸውን ገጠመኝና ልምድ፣ የዕለት ክንውኖች ተነስተው የሚሰሩ መልመጃዎችን፣ ግጥምን ወደዝርው ዝርውን ወደ ግጥም መቀየር፣ አንድን ፅሁፍ አሳምሮና አስረዝመው እንዲፅፉ በማድረግ ተግባራትን የመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን በተሻለ አተገባበር እንደነበራቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ፅህፈትን ለማስተማር ግልፅ መመሪያ ለተማሪዎች ከመስጠት አንፃር በግል ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች በግልፁ በማስተዋወቅ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠትና ስለአሰራሩ ግልፅ መመሪያ በመጠትና ከተማሪዎች ጋር በመግባባት ለትምህርቱ ትኩረት በመስጠት እንዲዘጋጁ ሲያደርጉ፣ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ግን ስለእለቱ ትምህርት ግልፅ በሆነ እና በበቂ ሁኔታ የዕለቱን ትምህርት ለተማሪዎች ሳያስተዋውቁ ትምህርቱን እንደሚያስጀምሩ በመረጃው ውጤት ተረጋግጧል፡፡ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት መገምገሚያ መስፈርት በማዘጋጀት ለተማሪዎች በማሳወቅ የምዘና መስፈርቶችን ለተማሪዎች በማሳወቅ የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በቀረበው መስፈርት መሰረት ሲመዘኑ፣ የመንግስ ትምህርት ቤት መምህራን ግን ተማሪዎችን በግል ከመመዘን ይልቅ አጠቃላይ የቡድን አባላቱ ምዘና ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ በመረጃው ውጤት ተረጋግጧ፡፡
- በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች አፋጣኝ ምጋቤ ምላሽ ከመስጠት አንፃር ያለው ሁኔታ ሲታይ፣ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች ሲሰሩ እየተዟዟሩ በመከታተል፣ ያልገባቸውን ነገር አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣ በትምህርቱም መጨረሻ በተገቢ ሁኔታ ማጠቃለያ በመስጠት ለተማሪዎች የተሻለ ድጋፍና ክትትል ሲያደርጉ፣ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ግን አጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ ያሉ ነገሮችን በወቅት በመመልከት በተወሰኑ ተማሪዎች ላይም በማተኮር እየተዟዟሩ ተማሪዎችን ለመርዳት ያደረጉት ጥረት አነስተኛ አንደነበር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተቻለው ለጥናቱ አጋዥ በሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች /በክፍል ምልከታ፣ የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና ለመምህራን በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ/ ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ እንደተቻለው በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ አማርኛ መምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴ አተገባበር በተመለከተ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡

5.2 አስተያየት

በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ9ኛ ክፍል መምህራን የፅህፈት ማስተማር ዘዴ አተገባበር በተመለከተ በአጥኚው የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

- በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንን የፅህፈት ትምህርት እቅድ ስንመለከት፣ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ፅህፈት ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ለማስተማር በአግባቡ ሲያቅዱ የሁለቱን ትምህርት አላማም ለተማሪዎች በግልፅ ሲያስተዋውቁ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ይህንን ተግባር ተረድተው በአግባቡ ቢተገብሩ የተሻለ ነው፡፡
- የፅህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ከመስጠት አንፃርም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በተለያየ መልክ የሚሰሩ የፅህፈት መልመጃዎችን ለተማሪዎች ሲሰጡ፣ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት ግን በተወሰኑ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የማተኮር ሁኔታዎችን በማሻሻል ቢተገብሩ የተሻለ ነው፡፡
- ተማሪዎች ስለሚሰሩት ስራ ግልፅ መመሪያ ከመስጠት አንፃርም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የሁለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች በግልፅ በማስተዋወቅ የሚሰሩትን ስራ እንዲረዱ የማድረግ የተሻለ ስራ ሲተገብሩ ተስተውሏል፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራንም ይህንን ትኩረት ሰምተው ቢተባበሩ የተሻለ ነው፡፡
- ፅህፈት መገምገሚያ መስፈርቶችን በማዘጋጀትና ለተማሪዎች በማሳወቅ፣ የግል ትምህርት ቤት መምህራን ተማሪዎችን በግልም፣ በቡድንም ተማሪዎች ሲመዝኑ ታይተዋል፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንም ተማሪዎችን በቡድን ብቻ ሳይሆን በግል ምዘና ላይም ትኩረት ቢያደርጉ በፅህፈት ትምህርት

ተማሪዎች ውጤታማ የሚሆኑ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ሲያገኙ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ይህንን ተረድተው በክፍል ውስጥ በመዟዟር ተማሪዎች ሲሰሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተማሪዎችን ጥያቄ በአግባቡ በማዳመጥ፣ ያልገባቸውን ነገር በማብራራትና በመፍታት ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጡ ከምልክት እና ከፅሁፍ መጠይቅ መረዳት ተችሏል፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራንም ለተማሪዎቻቸው ጠንከር ያለ ድጋፍ ቢያደርጉ፣ እኩል ተሳታፊ እና በነፃነት ሀሳባቸውን መግለፅ የሚያስችላቸውን ብቃት እንዲያዳብሩ ለተማሪዎች አፋጣኝ ምላሽ ቢሰጡ ጥሩ ነው፡፡

- በአጠቃላይ የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን በተማሪዎች የፅህፈት ትምህርት ወቅት ከመምህሩ የፅህፈት እቅድ አዘገጃጀት እስከ ማጠቃለያ ባሉት ተግባራት የተለያዩ ችግሮችን ሲተገብሩ ተስተውለዋል፡፡ በዚህ ረገድ ሌሎች ጠለቅ ያሉ ጥናቶች ቢካሄዱ ይበልጥ ችግሮችን ለማየትና የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ይቻላል፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች


ማረው አለሙ (1996) *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን(1987) በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የብጤ እርማት ተግባራዊነት እና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት፡፡

እንዳለ(1992) በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሑፋዊ መጋቢ ሚና፡፡

Alshahrani, A. (2011). Preparing ESL Students for University Level Writing: The Influence of (Unpublished Doctoral Dissertation) (Unpublished PhD Thesis). sR. (2003). *Task-Based Language Learning and Teaching.* Oxford: OUP_ (2004). Perspectives on Task-based Instruction: Understanding Our Practices, Arts.

Bariley, Kenneth (1987). Method of Social Research (3rd ed) Toronto Macmillen.

Block,Cathy Calling,(1997) Teaching the language arts Expanding thinking, through student Centered lnstruction.Bostonciallyn and Bucca.

Brown, J. and Rodgers, T.S (2002). *Doing Second Language Research*. Oxford: Oxford

Bruning, R. and Horn, C. (2000). Developing Motivation to Write. *Educational Psychologist,*

Byrne, D. (1988). *Teaching Writing Skills.* Longman: Longman Group UK LmitedCambridge: Cambridge University Press.D. C: Georgetown University Press.

Ellis, R. (2003). Task-Based Language Learning and Teaching. Oxford: OUP

Haregewain Abate (2008) "The Effect of Communicative Grammar on the Grammatical Accuracy of Students' Academic Writing: An Integrated Approach to TEFL." Addis AbabaUniversity: (Unpublished PhD Thesis).

Hyland, K. (2003) *Second Language Writing.* Cambridge: Cambridge University Press. *Instruction in Foreign Language Education: Practices and Programs.* Washington, intermediate French students. *International Journal of Applied Linguistics,* Vol. 156, 239- *International Journal of English Language Teaching,* Vol.3, (3), 40-52.

Magno, C. (2009). Self Regulation and Approaches to Learning in English Composition

Mills, N. A. and Péron, M. (2009). Global simulation and writing self-beliefs of college

Nunan, D. (1991). *Syllabus Design*. Oxford: Oxford University Press.

Payne, A.R. (2012). "Development of the Academic Writing Motivation Questionniare"

Prabhu. W. (1987). The structure of academic self-concept: The Marsh/Shavelson model, *Journal of Educational Psychology*, Vol.82

Qasim, S., Imtiaz, Z.and Alvi, U. (2014) Rivew of True Expermental Research Studies in Applied Linguistics. *Research on Humanities and Social Sciences:* Vol.4 (22), (146-149).

Raimes, A. (1983) *Techniques in Teaching Writing*. Oxford: Oxford University Press.

Richards, J. and Rodgers, T. (1983). *Approaches and Methods in Language Teaching*. *Science and Education* Vol. 41, (2), 64-72. social constructionism in a college technical writing class." Brigham YounUniversity

Willis, J. (1996). *A Framework for Task-based Learning*. London: Longman ltd. Writing.*TESOL Journal* Vol. 1, 1-16.

Zimmerman, B. (1994) "Collaborative, conversation, and communication: A qualitative study of social constructionism in a college technical writing class." Brigham Young University (Unpublished Doctoral Dissertation)

አበረቀች

# አባሪ አንድ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሒውማንስቲክ ቋንቋዎችና የአማርኛ ቋንቋ

# ሥነ-ጽሑፍ ፎክለር ትምህርት ክልፍል

## የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ

**መግቢያ፡-** በየዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታ ዋና አላማ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ኩሩዝ 2ኛ ደረጃ የግል ት/ቤትና በአየር ጤና 2ኛ ደረጃ የመንግስት ት/ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈት ማስተማር ዘዴ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር ለመፈተሽ ነው፡፡

የትምህርት ቤቱ ስም፡________________

1. የመምህሩ ስም፡________________
2. ምልከታው የተደረገበት ቀን ____________
3. ምልከታ የተደረገበት ሴክሽን/ምድብ/፡____________
4. በክፍሉ ያሉ ተማሪዎች ብዛት ________________
5. የትምህርቱ ርዕስ______________________
6. የክፍለ ጊዜው ርዝማኔ__________________
7. ትምህርቱ የተጀበረበት ሰዓት __________________
8. ትምህርቱ የተጠናቀቀበት ሰዓት________________

**ማሳሰቢያ ፡-** ለምልከታ የቀረበውን ቅፅ መልስ ለመሙላት ሁለት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን አዎ/ይተገበራል/

የለም/አይተገበርም/ የሚል ውክልና ያዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከአማራጮች አንዱን  ብቻ በመምረጥ በተመረጡት አማራጮች ባለው ሳጥን የ‹‹ ✓ ›› ምልክት በማስቀመጥ ይመልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ምልከታ ለማካሔድ የቀረቡ የቀረቡ ጥያቄዎች /ሐተታዎች | አዎ | ለም |
| --- | --- | --- | --- |
| 1 | የመምህሩ የፅህፈት ትምህርት እቅድ | | |
| 1.1 | መምህሩ/ሯ እቅድ አዘጋጅተው ክፍል ገብተዋል፡፡ | | |
| 1.2 | የትምህርቱን ዓላማ በሚገባ አስተዋውቀዋል፡፡ | | |
| 1.3 | የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመመዝገብ እቅድ አዘጋጅተዋል፡፡ | | |
| 1.4 | በክፍልና ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ስራዎችን ለመስጠት አቅደዋል፡፡ | | |
| 2. | የጽህፈት ችሎታን ለማሻሻል የሚያግዙ መልመጃዎችን ሰጥተዋል | | |
| 2.1 | የራስ ገጠመኝ እና ልምድ፣ የእለት ክንውኖች ወዘተ ተነስተው የሚሰሩ ስራዎችን ሰጥተዋል | | |
| 2.2 | የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን ግጥም፣ ድርሰት እንዲጽፉ ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 2.3 | ግጥምን ወደ ዝርው ዝርውን ወደ ግጥም ቀይረው እንዲሰሩ ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 2.4 | አንድን ጽሑፍ አሳጥረው /አስረዝመው እንዲጽፉት ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 3. | የመምህሩ/ሯ ፅህፈትን ለማስተማር ግልጽ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 3.1 | ስለ ዕለቱ ትምህርት ግልጽ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 3.2 | ተማሪዎች በግል በቡድንና በጥንድ ሲሰሩ ግልጽ መማሪያ ይቀርብላቸዋል፡፡ | | |
| 3.3 | የተሰጣቸው መልመጃ በግልጽ ሃሳባቸውን መግለጽ የሚያስችላቸው ነው፡፡ | | |
| 3.4 | በክፍልና ከክፍል ውጪ የሚሰሩ መልመጃዎች ይሰጣቸዋል፡፡ | | |
| 3.5 | አንዱ ተማሪ የሌላውን እያየ እንዲተራረሙ ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 3.6 | አስተዋጽኦ አዘጋጅተው ድርሰት እንዲጻፍ ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 3.7 | ተማሪዎች ሲሰሩ እየታዟዟሩ ይመለከታሉ | | |
| 4. | የመምህሩ/ሯ የፅህፈት ችሎታ ውጤት አያያዝ | | |
| 4.1 | መገምገምያ መስፈርት አዘጋጅተው ውጤታቸውን ይመዘግባሉ፡፡ | | |
| 4.2 | የምዘና መስፈርቶችን ለተማሪዎች ያሳውቃሉ | | |
| 4.3 | የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በማየት በግል ይመዝናሉ | | |
| 5. | የመምህሩ/ሯ ምጋቤ ምላሽ ማጠቃላያ መስጠት | | |
| 5.1 | በወቅቱ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ | | |
| 5.2 | ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣሉ | | |
| 5.3 | በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ማጠቃለያ ይሰጣሉ | | |

## አባሪ ሁለት

## ለመምህራን የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማንቲስ፣ ቋንቋዎችና የአማርኛ ቋንቋ

## ሥነ-ፅሁፍና ፊክሎር ትምህርት ክፍል

**በመምህራን የሚሞላ**

**ውድ መምህርት/ር**

የዚህ መጠይቅ አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመምህሩን ፅህፈት ማስተማር ዘዴን በመፈተሽ ንፅፅራዊ ጥናት ለማድረግ የሚረዱ መረጃዎችን ማስባሰብ ነው። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለቀርቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠቱ ከጥናቱ መሳካት መልካም ትብብር እንዲያደርጉልኝ ስል በአክብሮትና በትህትና እጠይቃለሁ። ትያቄዎችን በመመለስ ለሚያደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ፡- መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ ሦስት ክፍሎች የያዘ ነው። የመጀመሪያው አጠቃላይ የሆነ መረጃን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት ደግሞ አምስት አማራጮችን የያዘ እና አይ/አይደለም የሚል አማራጮችን የያዘ የምርጫ ጥያቄ ነው። በመሆኑም ከአማራጮቹ አንዱን በመምረጥ በመረጡት ቁጥር ትይዩ ባለው ሳጥን ውስጥ የ ‹‹✓ ›› ምልክት በማድረግ ይመልሳሉ። በክፍል ሶስት የቀረቡትን ክፍት ጥያቄዎች ሲሆኑ በፅሞና በማንበብ የሚመልሷቸው ናቸው።

<u>ክፍል አንድ</u>

**መመሪያ አንድ**፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ ስጡ።

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም፡_____________
2. ፆታ፡________________________ እድሜ፡ ________________
3. የትምህርት ደረጃ _____________ አገልግሎት ዘመን፡______________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ፡__________________

<u>ክፍል ሁለት</u>

**መመሪያ ሁለት** ፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች በአንዱ ትይዩ የ ‹‹ ✓›› ›› ምልክት በማስቀመጥ መልስ ይስጡ።

የምርጫዎቹ መግለጫ፡-

5. በጣም እስማማለሁ 2. አልስማማም

4. እስማማለሁ                1. ፍፁም አልስማማም

3. መወሰን እችላለሁ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ሳስተምር የተለያዩ የፅህፈት ማስተማርያ ዘዴዎች ን እጠቀማለሁ | | | | | |
| 2 | ፅህፈት ማስተማርያ ዘዴ ላይ በቂ ዕውቀት አለኝ | | | | | |
| 3 | የተለያዩ የፈጠራ ፅሁፎችን እንዲጽፉ ይደረጋል | | | | | |
| 4 | በግልና በቡድን የሚሰሩ ስራዎች እንሰጣለን | | | | | |
| 5 | ምጋቤ ምላሽ በወቅቱ ለተማሪዎች እሰጣለሁ | | | | | |
| 6 | የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል እመዝናለሁ | | | | | |

***መመሪያ*** ፡- ክፍል ሦስት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በፅሁፍ ያስፍሩ፡

1. ፅህፈት ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ዘርዝሩ፡፡

   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------
   -------------------------------------------------------------------------------------.

2. ፅህፈት ሲያስተምሩ የገጠመኞች ችግር ካለ በዝርዝር ያቅርቡ፡፡

   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------.

3. ፅህፈት ስለ ማስተማር ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት በፅሁፍ ያስፍሩ፡፡

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------------

# አባሪ ሶስት

# ለመምህራን የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የሂዩማንቲስ፣ ቋንቋዎችና የአማርኛ ቋንቋ

# ሥነ-ፅሁፍና ፊክሎር ትምህርት ክፍል

በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በግልና በመንግስት የ9ኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የመምህራን ጽህፈት ማስተማር ዘዴ እንዴት እንደሚተገበር ንጽጽራዊ ጥናት ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት መልካም ትብብር እንድታደርጉልኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ በቅድሚያ ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ መጠይቁን ለመሙላት ስለተባበራችሁኝ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ፡:

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- መጠይቁ ላይ ስምና ክፍል መጻፍ አያስፈልግም

- ✓ የምትሰጠው/ጪው መረጃ ከዚህ ጥናት ውጪ ለሌላ ተግባር አይውልም፡፡
- ✓ ተባብሮ መስራት አይፈቀድም

## አጠቃላይ መምሪያ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች አሉት፡- ክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት ደግሞ አምስት አማራጮችን የያዘ የምርጫ ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም ከአማራጮች አንዱን በመምረጥ በቀረቡት ቁጥር ትይዩ ባለው ሳጥነም ውስጥ የ ‹‹✓ ›› ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡ በክፍል ሶስት የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ የናንተ ነጻ አስተያት የሚጠይቁ ክፍት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## ክፍል አንድ

ቀጥሎ በቀረቡት መረጃ ነክ ጥያቄዎች የ ‹‹ ✓ ›› ምልክት በማድረግ መልስ/ሺ

ሀ. የትምህርት ቤትህ/ሽ ስም ________________

ለ. ፆታ፡ ወንድ ☐ ሴት ☐

ሐ. እድሜ 13-15 ☐ 17-20 ☐ 21 በላይ ☐

## ክፍል ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከ5-1 የተመለከቱ ክፍት ቦታዎች በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ለሚሰጡት ምላሽ ከቀረቡት አማራጮች በአንዱ ስር የ‹‹ ✓ ›› ምልክት በማድረግ መልስ/ሺ

5 በጣም እስማማለሁ

4. እስማማለሁ

3. መወሰን አልችልም

2. አልስማማም

1. ፍፁም አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ፅህፈትን ለማስተማር የመምህሩ/ሯ ዕቅድ | | | | | |
| 1.1 | መምህሩ/ሯ በእቅድ ያስተምራሉ | | | | | |
| 1.2 | የትምህርቱን ዓላማ በሚገባ ያስተዋውቃሉ | | | | | |
| 1.3 | የክፍሉን ሁኔታ በሚገባ ይቆጣጠራሉ | | | | | |
| 1.4 | አቅደው መረጃ መሣሪያ ያዘጋጃሉ | | | | | |
| 1.5 | በግልና በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን ይሰጣሉ | | | | | |
| 2. | የጽህፈት ማስተማር አተገባበር | | | | | |
| 2.1 | ስለ ዕለቱ ትምህርት መመሪያ ይሰጣሉ | | | | | |
| 2.2 | የሚሰጣችሁ መመሪያ ሃሳባችሁን መግለጽ ያስችላችኋል | | | | | |
| 2.3 | አንዱ ተማሪ ሌላውን እያየ እንዲተራረሙ ያደርጋል | | | | | |
| 2.4 | የተለያዩ የፈጠራ ፅሁፎችን እንዲጽፉ ያደርጋሉ | | | | | |
| 3. | የመምህሩ/ሯ ውጤት አያያዝ | | | | | |
| 3.1 | የመገምገሚያ መስፈርት አዘጋጅተው ውጤት ይይዛሉ | | | | | |
| 3.2 | የምዘና መስፈርቶችን ለማስተማሪያ ይጠቀማሉ | | | | | |
| 3.3 | ለእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በግል ይመዘግባሉ | | | | | |
| 4. | የመምህሩ/ሯ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | | | | | |
| 4.1 | ለተማሪዎች ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ | | | | | |
| 4.2 | ከተማሪዎች የሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣሉ | | | | | |
| 4.3 | በጽህፈቱ መጨረሻ ማጠቃለያ ትምህርት ይሰጣሉ | | | | | |

## መመሪያ ሶስት

ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በጽሁፍ አስፍሩ

1. መምርሩ/ሯ ጽህፈት ሲያስተምሩ የሚያከናውኑትን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------.

2. ጽህፈት ስትማሩ ያጋጠሟችሁ ችግሮችና ዘርዝሩ መፍትሔዎቻቸውን ዘርዝሩ፡፡

----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------.

3. የመምህራችሁን ጽህፈት የማስተማር ስነ ዘዴ ማስተማር ዘዴ የመምህሩን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ዘርዝሩ፡፡

----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------.

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታችን ስም እና ፊርማዬን ያስቀመጥኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ የጥናት የራሴ ስራ እና በጥናቱ ውስጥም የተጠቀምኳቸው ጽፎች ምንጭ በሙሉ በትክክል የተጠቀምኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- እጅጋየሁ ተሾመ

ፊርማ፡______________________

አድራሻ፡-አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህማንስቲክ ቋንቋዎች ጥናትና ጋዜጠኝነ፤ ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ቀን____________________________